ሁሉም ስፍራ ላይ ድንግዝግዞች አሉ። ይህ ድንግዝግዝ ዘመን አልፎ ብሩህ ቀን ሲመጣ የተፈጥሮ ጥበብ መመርመሩ የሚቀር አይመስለኝም። አሁን ተረት ተረት የሚመስሉ ሁሉ ድሮ እውነታነት ነበራቸው። የተዋነይም ከዚህ የተለየ አይደለም። ጥበብ ከተረት ተረት ከመቆጠሩ በፊት እውነት ነበር። እውነት ወደተረትነት የሚመጣው ግን በድንግዝግዝ ዘመን ነው። ይህ የድንግዝግዝ ዘመን አልፎ የወገግታ ዘመን እስኪመጣ መጸለይ መልካም ነው።" ካሉ በኋላ አከሉበት።

"ይህን ታሪክ ያመጣሁት በከንቱ አይደለም። ከአስማት ነጻ የሆነው የተፈጥሮ ጥበብ ከቅርብ ዘመን ወዲህ መደገሙን ለማስረዳት ነው። ቢሰውር ደግሞታል። ምሥጢሩ ከእሱ በኋላ በነበሩ ሊቆች እጅም አለ ለማለት ነው።" ብለው የቢሰውርን ከተዋነይ እያጻጸሩ ቀጠሉ።

"ይህ ከተዋነይ ታሪክ ጋርም ይጻጻራል። በአፈ ታሪክ ስለተዋነይ ሀገር የሚያወራን ደግሞ ተመልከቱ! ተዋነይ በንጉሥ እስክንድር ዘመን ነበር። በዚህ ወቅት ከንጉሡ ሚስት ጋር በፍቅር ወደቀ። በመሰውር ሰውሮ ደቅ ይዟት ገባ። ደቅ መግባቱ በሀገሬው አንደበት ተወራ። ከአዝማሪዎች ጆሮም ደረሰ። ያን ጊዜ የሕዝብ ዐይንና ጆሮ አዝማሪዎች ነበሩ። በሀገር ሲወራ የሰሙትን ግጥም ገጥመው ውስጡን

በቅኔ መጥነው በዜማ ቀምረው በቀጭን ጭራ ይገልጡታል። የተዋነይ ጉድም የተገለጠው ባዝማሪ ጭራ ነበር። ንጉሡ የሚስታቸውን መጥፋት በግልጽ ለመናገር ባፈሩበት በዚያ ወቅት አዝማሪ መሰንቆውን እየገዘገዘ ከንጉሡ ፊት ቀረበ።

ንጉሡ ውዳሴ ሲጠብቁ አዝማሪው ገመናቸውን ነገራቸው። ንግሥቷ ለፍቅር ተሰውታ ነበር። ለተዋነይ ፍቅር ስትል ደቅ ነበረች።

“ኂሩት እጇን ተሰብራ ከመኻሉ

ደቅ አለች አሉ ደቅ አለች አሉ።”

ሲል ደቅ መኖሯን አበሠራቸው። ቢመጡ ከተዋነይ ጋር በፍቅር ወድቃ ደረሱ። በተዋነይ ላይ እርምጃ ሲወስዱ ሲዘጋጁ በስዋሬ ሰውሮ በጢስ ቀለበት ከደቅ ይዟት ወጣ ሲሉ ይተርኳሉ። ይህ አፈ ታሪክ ይሁን በወቅቱ የተፈጠረ ክስተት አሁን ድረስ በውል አልተመረመረም። የአብነትና የቢሰውር የፍቅር ምሥጢር ግን የቅርብ ዘመን ታሪክ ነው። ግልፕ ለማድረግ የአብነት ሀገሯ አቸፈር ይባላል። አቸፈር ከባሕር ዳር ጋር ኩታ ገጠም ነው። በዚች ወረዳ አቤ ጉበኛ የሚባል ደራሲ ተፈጥሮባታል። አልወለድም በሚለው መጽሐፉ ሀገር





ያውቀዋል። አቸፈር ከግእዝ ባለቅኔዎችም በኩል ሊቆች ነበሯት። ባለ ቅኔው ደመናው ገሰሰ የአቸፈር ሰው ነበሩ። ከዚህ ላይ የስዋሬውን ምሥጢር የአቸፈሩ ደመናው ገሰሰ የሠሩት መስሏችሁ ደመናው ገሰሰን እንዳትጠረጥሩ። በእርግጥ ደመናው ገሰሰ የማዕበል ፈንቴ መምህር ናቸው። ሊቁ ማዕበል ፈንቴን በሊቅነት የቀረፁ ቢሆንም በቅኔ ቤት ግን የማዕበል ፈንቴን ያኽል የገነነ ስም የላቸውም። ደመናው ገሰሰን እንዳትጠረጥሩ። በስዋሬው በኩል የሉበትም። ቢሰውር ግን መናኛ ተማሪ ነበር። እርግጥ ነው! ጥበብ ባልባሌ ሰው መዳፍ እንዳለች መዘንጋት የለባችሁም።” ብለው ቀጭኗንና ጠባቧን መንገድ ይዘው ወደሰሜን መስዕ ሊሄዱ እያማተሩ

“በግሌ ግን የስዋሬ ጥበብ ብቻውን በውል ተፈላጊ ጥበብ አይደለም። ተሰውሮ የሰውን ገመና መመልከት ምንም አይሠራም። በዚያ ላይ ሰው ከተሰወረ ምን ይበላል? ምን ይጠጣል? የሚል ጥያቄ አለ። በዚያ ላይ እንደተሰወሩ ቢሞቱ መልካም አይደለም። ለዚህ መልስ መስጠት ያስፈልጋል። ከተሰወሩ በኋላ ምግብ ስለሚያስፈልግ መናውን መያዝ ግድ ነው። ቢሰውር ከተሰወረ በኋላ ጭንቅ ገጥሞት ነበር። ልጅቷን ይዞ ከተሰወረ በኋላ የሚልሰው የሚቀምሰው አጣ። ሲጨንቀው ከስዋሬ ወደ ተከስቶ መጣ። ከልጅቱ ጋር በፍቅር ቢቀጥልም በስዋሬ መኖሩ ግን ከጊዜ በኋላ ከሸፈ።” ብለው



Scanned with CamScanner

ጣታቸውን ከመጽሐፉ ሲያነሡ ገሞራው በስርቅታ ወደሁለተኛው ዐምድ ተመለከተ:: ከመጀመሪያው ገጽ ላይ ኀብስተ መና ጽሑፍ የሚል ጽሑፍ ተለጥፏል:: ቀና ብለው ሰማዩን ተመለከቱ:: ድቅድቁ ጨለማ እየነጋ ነበር::

"በዚህ ሳምንት ውሎ አዳሬ ክርክር ሁኗል:: እናንተ ጥቂት ዕረፍት ወሰዱ:: ማታ እመጣለሁ::" ብለው መጽሐፉን አጠፉ:: ሁለቱ ተማሪዎች ግጥሟን እየመዘገቡ ከዐራት ዐይናው ጥቂት ገሸሽ አሉ:: ምን ነበር ያሉ የቢሰውር ጓደኞች?

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)





## ፳፫

### ተከስተ ለምን ሞተ?

ጠቢባኑ ለጉባኤ ሲቀመጡ የዛሬውን ጉባኤ ዐራት ዐይናው እንዲመሩት ተመረጡ:: በዚች ቀን የስዉሩ ዓለም ሴቶችም በጉባኤው ተሰይመዋል:: መናው በእጃቸው፣ ጥበብ በማጀታቸው የሆኑ የስዉሩ ዓለም ሴቶች ከጠቢባኑ ራቅ ብለው መሬት መሬት እያዩ ጉባኤውን እየተሳተፉ ነበር:: የስዉሩ ዓለም በር እንዲዘጋ አብረው ወስነው ስለነበር ያንን ለመሻር ወይም ለማጽናት ድጋሜ ተጠርተው መጥተዋል::

በዚህ ጉባኤ ዐራት ዐይናው የመጀመሪያውን ንግግር ጀመሩ:: የጠቢባኑን ጆሮ የሳበ ንግግር ነበር::

"እኔ እኒህ ልጆች ከእኛ ጠቢባኑ ጋር ይኑሩ የምለው ሊቃውንት ስለሆኑ ብቻ አይደለም:: ወደመኻል ሀገር ተመልሰው ቢሞቱ በሰማይ ቤት ለሁለተኛ ጊዜ በነፍሰ-ገዳይነት እንደምንጠየቅ አስቤ ነው::" አሉ ሳያስቡት ወደ ደቀኛው እየጠቆሙ:: ደቀኛው ቀና ሲሉ ከዐራት ዐይናው ጋር ዐይን ለዐይን ተጋጩ:: በነፍሰ ገዳይነት እንጠቃለን እያሉ ሳያስቡት ደቀኛውን በአመልካች ጣታቸው እየጠቆሙ ሳለ ደቀኛው ሲደርሱባቸው ዐራት ዐይናው ክው ብለው ደነገጡ::

"ነፍሰ ገዳይ? እኔ ነኝ ነፍሰ በላው ወንበዴ? ነፍሰ ገዳይ እኔ?" አሉ ደቀኛው በጣታቸው ወደዐራት ዐይናው እየጠቆሙ፡፡ "አዎን! በተከስተ ሞት በሰማይ ቤት ይጠየቃሉ፡፡ ቀጥቅጠው ባይገድሉትም መናውን ወደ ቤተ መንግሥት ይዞ መሄድ የለበትም ብለው ለሞት አሳልፈው የሰጡት ርስዎ ነዎት፡፡ አሁን ደግሞ እኒህ ሊቆች ወደመኻል ሀገር ተመለሰው ይሞቱ ዘንድ ሞት እየፈረዱባቸው ነው፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው ገሞራውና ታሪኩ ወደ ጠቢባኑ ዓለም ገብተው እንዲኖሩ አጥብቀው እየሞገቱ፡፡

"ተው እንጂ ዐራት ዐይናው! በጠቢባኑ ፊት ዕርቃኔን አታቁመኝ፡፡ ሰማይ ቤቴን አትዝጋው፡፡ ነፍሰ ገዳይ አድርገህም አትሳለኝ፡፡ የተከስተን ነገር ቀደምት ጠቢባን ቢያውቁትም ቅሉ ከደርግ ዘመነ መንግሥት በኋላ ስዉሩን ዓለም የተቀላቀሉ ላያውቁት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በደንብ ላብራራላቸውና ፍርዱን ይስጡ፡፡ አንተ እንዳልኸው እኔ ነፍሰ-በላ ከሆንሁ በሕይወት እያለሁ ወደመኻል ሀገር ሄጀ ተዘቅዝቄ እሰቀላለሁ፡፡" ብለው መናገር ጀመሩ፡፡

"እግዜር ያሳያችሁ ወንድሞቼ! እኅቶቼ የእኛ ቤዛዎች የስዉሩ ዓለም ሴቶች! እግዜር ያሳያችሁ!፡፡ የተከስተን ነገር እናንተም ታውቃላችሁ፡፡" ብለው ጀመሩ፡፡





"ተከስተ መጀመሪያ የደብረ ኤልያስ የቅኔ ተማሪ ነበር፡፡ በጥበብ በኩልም ከደቂቀ ተዋነይ እስከ ደቅ እስጢፋ የጠቢባንን በር አንኳኩቷል፡፡ ለጥበብ እንደ ፍየል ቀንድ የቆመ ልብ ነበረው፡፡ ጃንሆይ የጃማይካ አምላክ ተብለው እንዲጠሩ የረዳቸው ተከስተ ዝናቡ ነበር፡፡ ወደ ስዉሩ ዓለም የመጣው በዘመነ ጃንሆይ ነበር፡፡" ብለው ታሪኩን ከዘመን አናክሰው ቀጠሉ፡፡

"ከሥር ሳመጣው ጃንሆይም ኢትዮጵያን ጨምሮ ድፍን አፍሪካን የመግዛት ፍላጎት ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጎን ከብዙ ጠቢባን ደጅ እድርሳለሁ፣ ጥበባቸውን እወርሳለሁ፣ እንደ ተዋነይ ሞትን ገዝቼ በትረ-መንግሥቴን እንደጨበትሁ በዚች ሀገር እኖራለሁ የሚል በጥበብ በኩል የሚጨበጥ ተስፋ ነበራቸው፡፡ ተስፋቸው ከተከስተ ጋር ተቀጨ፡፡" ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ እንባ ቀደማቸው፡፡ ወይራው በርረው ተነሥተው አስቀመጧቸው፡፡

"ይቀመጡ! ይቀመጡ! ለታሪኩማ ዐራት ዐይናው አሉልን፡፡ እሳቸው ያስረዱናል፡፡ ርስዎ ይቀመጡ፡፡" ብለው ሊያስቀምጧቸው ዐራት ዐይናው አፈፍ ብለው ተነሥተው ቀጠሉ፡፡



Scanned with CamScanner

“እንደተባለው የጃንሆይ ሕልም የተቀጨው ከተከሰተ ጋር ነበር። ተከስተ ባጭር እንዲቀጭ ያደረጉት ደግሞ ደቀኛው ናቸው።” አሁንም መልሰው ከሰሏቸው። ደቀኛው ደማቸው ፈልቶ ሲነሡ ሲንገዳገዱ ወይራው እንደወይራ በጠነከረ መዳፋቸው ሰቅዘው ይዘው አላነቃንቅ አሏቸው።

ዐራት ዐይናው ግን ቀጠሉ።

“ጃንሆይ በሰባት ወር የማሕፀን ቆይታቸው ከደቂቀ ተዋነይ የመነጨ ሀገር በቀል እሳቤን ይዘው ተወለዱ። ከንግሥናቸው በኋላ በእናታቸው ሆድ ውስጥ ሰባት ወር ብቻ የቆዩት ለንግሥና ካላቸው ጉጉት የተነሣ ነው የሚል ሐሜት ተወርውሮባቸዋል። ዘጠኝ ወር ሳይጠብቁ ፈጥነው ስለተወለዱ ሐበሻ የፈጠረው ልበ-ወልድ ነበር። እውነታው ግን ከሐበሻ ሐሜት የራቀ ነው። በሰባት ወር መወለድ ደግሞ ብርቅ አይደለም። የአቡሻህር ሊቆችም በሰባት ወር ልደት መኖሩን ያምናሉ። እናም ጃንሆይ ለንግሥና ቸኩለው በሰባት ወር ተወለዱ የሚለው ቀልድ የዘመኑ ፌዝ ነበር። ባይሆን ጃንሆይ እድሜአቸው ለራስነት ሳይደርስ፣ ንግሥት ሳለች የውስጥ ንጉሥ መሆናቸው ቅሬታ ፈጥሮ ነበር። ንጉሡ ግን ያለምንም ግርግር ንግሥናን ተቆናጠጡ። ከራስነት ወደርእሰ ብሔርነት ተመነደጉ። በዚህ መኻል የጣሊያን ወረራ





ተፋፋመ። ጃንሆይ ሲሰደዱ ሲያቆበቁቡ ሊቃውንቱ ስደቱን አጣጥሉት። ጃንሆይ ግን ጆሮ ዳባ ልብስ ብለው ቼ ፈረሴ አሉ። ኢትዮጵያ የጋላበው ፈረስ እንግሊዝ ጣላቸው። በስደት እያሉ ከጃማይካውያን ጋር ማኅበር እስከመመሥረት የደረሰ ፍቅር ጀመሩ። ጥቁሩ ሰው ከጥቁሮች ጋር በማኅበር ተዛመዱ። በአፍሪካዊነት ተጋመዱ። ከስደት መልስ ግን ጃንሆይ ዝም አላሉም። ሊቃውንቱን ለመሰብሰብ ፈለጉ። መጀመሪያ ጃንሆይ ወደ መደቆሻው ደብዳቤ ላኩ። መደቆሻው የጃንሆይ የነፍስ አባት ነበሩ። ቅድመ ስደት ከቤተ መንግሥት ወጥተው መንነው ገዳም የገቡ ናቸው። መልእክት ሲደርሳቸው ጎንደር ውስጥ “እማማ ገዳም” ገብተው እንደገና ተደበቁ። የሴት ወይዘሮዎችን አማላጅነት ቢልኩ “ገጸ አንስት” አላይም “ድምፀ ብእሲት” አልሰማም ብለው አመፁ። ከሊቃውንቱ ክፍል ቢላክ “በዚች ዘመን ዐይናማ ሊቆች አልቀዋል። ሊቆች በእምዬ ምኒልክ ዘመን ቀርተዋል” ሲሉ ከቤተ መንግሥት በተኮለኮሉ ሊቃውንት ተሳለቁ። ካራቱ ማዕዘን ሊቃውንት እየተመራረጡ ወደ መደቆሻው ቢላኩ አሻፈረኝ አሉ። ወደ መጨረሻው ግድም በላይ ዘለቀ ተላከ። አባ ኮስትር “እማማ ገዳም” ሲደርስ መነኩሳቱ ከየበዓታቸው ወጥተው ተቀበሉት። መደቆሻም ለጀግንነቱ ክብር ቡራኬ ሰጡት። ነገር ግን አባ ኮስትር

ስለማውረድ እንዲያብራራ ሲጠየቅ ብድግ ብሎ ከሲቃውንቱ መኻል ተሰወረ። መሰወሩ ግን የፍርሐት አይደለም። እንደ ደቂቃ ተዋነይ መሰወር እችላለሁ። ዝናም ማዝነብ የንዑስ ደቀ መዝሙር ማዕረግ ነበር ሲላቸው ነው። እሱ እንደ ተሰወረ ሲቃውንቱ በቅንዐት ነደዱ። ከስዉሩ ዓለም ሲሄድ ጊዜ አገው መስኳቸው "አገው ልቡ ዘጠኝ ልቡ ዘጠኝ" እያሉ ረገሙት። በእርግጥ ለተከስተ ዘጠኝ ልብ ባይኖረው ቅሉ ዘጠኝ ጥበባት ነበሩት። ስድስቱ የተዋነይ ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ የማዕበል ፈንቴ ዘዋሸራ ነበሩ። በዘጠኙም ይጠቀምባቸው ነበር። ጠቢባኑ ጮማ ሲቆርጡ ጠጅ ሲያንቆረቁሩ ለነባብተው ሲበተኑ ተከስተ ተመልሶ ተከሰተ። ከቅኔ ቤት እንጂ ከስዉሩ ዓለም እንደመጣ ያወቀ ማንም አልነበረም። ጃንሆይ አደግድገው ተቀበሉት። ከውጪ ሀገር የተነሷቸውን ፎቶ ግራፎች አስጎበኙት። እንደኢትዮጵያዊ ዜጋ ሳይሆን እንደውጪ ሀገር እንግዳ አክብረው አጓደው አስተናገዱት። በተለይ ሉሉ የሚባለው ውሻቸው ከእግሩ ላይ ሳይሸናበት በመቅረቱ ተደመዋል። ተከስተም ፈገግ እያለ ቤተ መንግሥቱ መንግሥቱን በፍሥሓ ሲጎበኝ አመሸ። በቤተ መንግሥቱ የግብር ቤት የተኮለኮሉ ከፊል ጠምጣሚዎችን እየተመለከተ ሲመንናቸውም ነበር እሉ። ከዚያ ሁሉ ጠምጣሚ የሁለተኛዋን የሰማይ መስኮት ምሥጢር የሚያውቅ እንደሌለ





ሲያስብ "ከመጠምጠም መማር ይቅደም" እሉ የሀገሬ ሊቆች? እውነታቸውንኮ ነው። እኒህ ፊት ለፊት የተኮለኮሉ ሊቆች መጠምጠም እንጂ በጥበብ መቅደም አያውቁም። ያ ቢሆን ኑሮ ትልቁ የአፍሪካ የቁርጥ ቀን ልጅ ከቅኔ ተማሪ ድረስ ወርደው የቅኔ ተማሪ ጓደኛ ባላደረጉ ነበር እያለ ሲደመም አምሽቶ ከቤተ መንግሥቱ ክፍል ከፈረንሳይ የመጣ አልጋ ሊሰጠው አጉዛ አምጡ ብሎ ከበር ተጋድሞ በሁለተኛዋ የሰማይ መስኮት ሲፈላሰፍ አደረ። ይች መስኮት የዝናም መስኮት ናት። በሄኖክ ቀመር ትታወቃለች። ዝናም የምትሰጠዋ መስኮት እሷ ናት። የእሷን ቀመር ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ተከስተ ይቺን ያወቅ ስለ ነበር በመስኮቷ ተፈላሰፈ። መጀመሪያ ለሙከራ ያኽል አዲሳባን በውሽንፍር መታት። ከዚያም የነፋሱን አውታር ወደኦጋዴን ወነጨፈው። የተጠማው የኦጋዴን ምድር ለአፍታ ረሰረሰ። ዋቢ ሸበሌ ከወሰኑ አልፎ የጎዴን ከተማ ሲያስጨንቃት አደረ። ከዚያም በሰላም ተኝቶ አድሮ ሲነጋጋ ሲል የጀማይካን የምድር ወገብ ለክቶ የሁለተኛዋን የሰማይ መስኮት ሲለካው ከሐሳበ ሰማይ ወምድር ጋር ተገጣጠመለት። ሰማዩን በሐሳበ ሰማይ፣ ምድሩን በሐሳበ ምድር ለክቶ የረጋውን ደመና በነፋስ አውታር ገጨው። ንጉሡ ወደ ጃማይካ ከመሄዳቸው ቀደም ብሎ የጃማይካ ደመና በነፋስ ሲገጭ የጃማይካ ሰማይ

ጠቋቆረ:: ፀሐይ ብርሃኗን አጣች:: ጨለማ ተጋረደ:: ጃማይካውያን በፍሥሐና በፍርሃት ተዋጡ:: ፍርሐታቸው የጨለማው ክብደት ያመጣው ነበር:: ፍሥሐቸው ደግሞ ለሰባት ወራት ያኽል ዝናም ጠብ ሳይል ኑሮ በዝናም መጥለቅለቃቸው ነበር:: በጃማይካ ዝናም መጣሉን ሲያረጋግጥ ጃንሆይ ወደጃማይካ እንዲያቀኑ ነገራቸው:: ወደጃማይካ በረሩ:: በዚያች ዕለት በጃማይካ ሰማይ ዝናሙ እንደጉድ ወረደ:: በዚያች ቀን ደመናው ሲያንዣብብ ቆይቶ ጃንሆይ ከመነሣታቸው ቀደም ብሎ ጃማይካ ውቅያኖስ በውቅያኖስ ሆነች:: በጃማይካ ሕዝብ ዘንድ ጃንሆይ አምላክ መስለው ታዩ:: ጃማይካውያን ጃንሆይ ዝናም ያወረዱ መስሏቸው የጥቁሮች አምላክ ሰው መስሎ ወደ ቤታችን መጣ! ሲሉ ገለጧቸው:: ያን ጊዜ ጃንሆይ 'ተከስተ! ተከስተ! ጠቢቡ በትክክል ተከሰተልኝ!' እያሉ በፍሥሐ ከነፉ:: አሁን ልቤ የወደደችውን 'አገኘሁ' እያሉ ያችን እጃቸውን እያወናጨፉ ፎከሩ:: የመጀመሪያ ስሙ ቀጸላ ነበር:: ተከስተ ወደሚል ስም ተለወጠ:: ተከስተ የጥበብ ስሙ ነው::" ፋታ ወስደው ጨመሩበት::

በመካከል ጠቢቡ ሖረ ተነሥተው "እንዲያ ነው! እሰይ የእኔ ሊቅ! እሰይ የእኔ ዐራት ዐይና! አንተ ብትሞት ኑሩ የአንድ ሊቅ ሞት ኢትዮጵያ ስንት ጊዜ ትሞት ነበር:: የአንዲት ሀገር ሞት ጭምር ነው::" ሲሉ አወደሷቸው:: ዐራት ዐይናው ግን ቀጠሉ::

"ጃንሆይም በጃማይካ ሰማይ ሥር መዓት ዝናም በወረደበት ሌሊት ፍሥሐቸው ገንፍሎ እንቅልፍ እምቢ ብሏቸው ከአልጋቸው ወርደው ክፍላቸውን ዘግተው ወደ ሰገነት ወጥተው የጃማይካን ወንዞች ሲቃኙ አመሹ:: በጎርፍ የሰከሩ ወንዞች በአያሌው ይገማሸሩ ነበር:: ሰማዩ አሁንም በደመና ጢቅ እንዳለ ነበር:: ዐይናቸውን ወደላይ ቀና አድርገው "ያ መናጢ የቆሎ ተማሪ ከፈጣሪ ጋር ተጣልቶ ይችን ሀገር በንፈር ውኃ እንዳይቀቅላት ፈራሁ? አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ! ለዚች ደሃ ሀገር እራራላት፤ እዘንላት:: እኛም በወጣነው እንዳንቀር ወደ ዙፋናችን በሰላም መልሰን" ሲሉ በንጉሣዊ አነጋገር ራሳቸውን አንቱ ብለው ጸለዩ:: ጥቂት ቆይቶ ሰማዩ እየገለበ ደመናው እየገለጠ ሄደ:: ከሰገነት ወርደው ሰዓታቸውን እየተመለከቱ ወደአልጋ ክፍላቸው አዘገሙ:: በሌሊት ልብስ ብቻ ነበሩ:: ወደ ክፍላቸው ገብተው ከረጅሙ አልጋቸው ላይ ሺበለሉ ኩርትም ጭብጥ ብለው ወፍራም ጉቶ አከሉ:: ከጀማይካ መልስ ግን ፍሥሐቸው ሊቀጥል አልቻለም::" ብለው አሁንም ወደደቀኛው አማተሩ::


Scanned with CamScanner

“ከጃማይካ ሲመለሱ ለተከስተ የተለመደውን መደለያ ሰዓትና ራድዮ ይዘውለት መጥተው ነበር።

ተከስተ ግን ከቤተ መንግሥት አልነበረም።” ዐራት ዐይናው ቁንጽል ታሪክ አይወዱም።

“ከቤተ መንግሥት ወደ ጠቢባኑ ዓለም ሲመለስ ዐባይ ሸለቆ ውስጥ ሽፍቶች ቀጥቅጠው ጣሉት። የመኪንንቱ ስዉር መዳፍ ነበረበት። ለጥበብ የተሠዋ የመጀመሪያ የጥበብ ሰማዕት ለመሆን በቃ። ከዚያ በኋላ ጃንሆይም ተንኮታኮቱ።” ወደደቀኛው ዞወር ብለው “ሊሞት የቻለው በደቀኛው ክፋት ነው። መናውን ይዞ ሂዶ ቢሆን መልአከ ሞትን ማሠር መገዘት ይችል ነበር። ደቀኛው ከለከሉት። ለሞት ተላልፎ ተሰጠ። አሁን ደግሞ እኒህን ልጆች እየተቃወሙ ነው። ገዳማዊው ወይራው ሳይቀር ደቀኛውን ተከትለው መግባት የለባቸውም እያሉ ነው። በሉ ፍረዱ።” ብለው ቆጭ ሲሉ ደቀኛው እሳት ለብሰው ሊነሡ ሲሉ ከሴቶች አንዷ ፈጠን ብላ ተነሥታ “ተዉ ከርታቶች! ጠቢባኑ ሆይ! ታሪክ አያጋጭም ባለፈው ታሪክ አትጋጩ። ከተከስተ ሞት በኋላ ጃንሆይ ይቅርታ ሊጠይቁ ይሁን የሞት መግቻውን ፈልገው ወደ ስዉሩ ዓለም መጥተው ነበር። ተከስተ በምን ምክንያት እንደሞተ የሚጠቁም ደብዳቤ ከእኔ እጅ ይገኛል። ጃንሆይ





ሊመጡ ያመጡት ነው። ወደ ስዉሩ ዓለም መግባት ሊያቅታቸው ከኪዳነ ምሕረት ዋሻ ጥለውት የሄዱት ደብዳቤ አለ። ደብዳቤው ተነቦ ጥፋቱ የማን እንደ ሆነ ይታወቃል።” ብላ አስታራቂ ሐሳብ አፈለቀች። ደቀኛው እያለቀሱ ወደ ቤታቸው ገሰገሱ። ዐራት ዐይናውም ለነገሞራው ብለው ደቀኛውን በማሳዘናቸው እንባቸው “ጀድድድ” ሲል ተሰማቸው። ጠቢባኑ ሰውነታቸው ሙቆ ተለያዩ። የእነገሞራው ጉዳይ መፍትሔ ሳያገኝ ከእነ አካቴው ተረሳ።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



Scanned with CamScanner

# ፳፬

ተጊናይ

ዐራት ዐይናው ተናደው እንደተመለሱ ገሞራው ታሞ ተኝቶ ደረሱ።

"ምን ነው እንቅልፍ አልወጣልህ?" አሉ ዐራት ዐይናው።

"እንቅልፍ አይደለም። ትናንት ጥርሴን ቅዝቃዜ አግኝቶት ሕማሙ ተቀስቅሶብኝ ነው።" አለ ገሞራው።

"አይዞህ! በርታ በል።" ብለው "ታሪኩ ወዴት አለ?" ሲሉ ታሪኩ ዐይኖቹን በእጁ ጨብጦ መጣ።

እንደተለመደው ከዐለቱ ላይ አረፍ እንዳሉ

"ደቂቀ ተዋነይ ወደ ስዉሩ ዓለም እንዳትገቡ የሚከለከሉት ወደድው አይደለም። እናንተ የቀለም ቀንድ ስለሆናችሁ እንደ ተዋነይ የመናውን ቁራሽ ወደመኻል ሀገር ይዘው ይሄዳሉ እንጂ እኛን መስለው ላይኖሩ ይችላሉ ብለው ነው። አትፍረዱባቸው።" አሉ ዐራት ዐይናው።

"እኛ እንደ እሱ አናደርግም። ነገር ግን ወደ መኻል ሀገር ብንወስደው ምን ጉዳት አለው?" አለ ታሪኩ።





"ጉዳትማ አለው! የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና በልቶ ያልጠገበ ሕዝብ ነው። ይህንን የመሰለ ሀገር በቀል ጥበብ ለባዕዳን አሳልፎ ይሸጠዋል እያሉ ይፈራሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ስዉሩ ዓለም ማንም እንዳይገባ የከለከሉትም ለዚሁ ነው። ምሥጢር ለመጠበቅ። በዚያ ላይ በተዋነይ ቂም ይዘዋል። የመናውን ምሥጢር ከስዉሩ ዓለም ወደ ገሀዱ ዓለም መውሰዱ አናዷቸዋል።"

"እንዴት?" አለ ታሪኩ ቀለሙ ዐይናቸውን እያርገበገቡ ቀጠሉ።

"ተዋነይ ወደሴቶች የጥበብ ዓለም ከመምጣቱ በፊት የቅኔ ሰው ነበር። ብላቴና ልጅ እያለ መወድስ የሚፈጥር ጭንቅላት ነበረው። ከዚህ ጎን ለጎን በሀገራችን ውስጥ የጠቢባን ዓለም መኖሩን ሰማ። ምሥጢሩን ቀደም ብለው ወደዚህ የመጡ ባሕታዊ እንደነገሩት ይወራል።" ሲሉ ትርክቱን ከሥር ሳቡት።

"የአመጣጡ ምሥጢር ወዲህ ነው! ያን ጊዜ እኒህ ሴቶች እንዳሁኑ ራሳቸውን ሰውረው ብቻ አይኖሩም ነበር። በቁጥር ጥቂቶች ስለሆኑ ብዙ ተባዙ ባለው መለኮታዊ ቃል መሠረት ዘራቸውን ለማብዛት ወደገሀዱ ዓለም ብቅ እያሉ በዳንግላ ገዘያ ዘወር ዘወር ብለው ወጣቶችን እየመለመሉ ወደ ሴቶች

የጥበብ ዓለም ያመጡ ነበር፡፡ ይህን የሰማው ተዋነይ ገበያ ወጥቶ ከጠቢባን ዓለም የመጡ ሴቶችን መፈለግ ጀመረ፡፡ "ደቅ ከጠቢባን ዓለም የመጣችሁ እኔ አለሁ በሉኝ አዋጅ አዋጅ እኔ አለሁ በሉኝ!" እያለ ገበያ ለገበያ ሲለፍፍ ያበደ መስሏቸው የተሳለቁበት እንደ ነበሩ ይተረካል፡፡ እኒህ ሴቶች ግን ራሳቸውን ደብቀው የተዋነይን ሁኔታ ሲመለከቱ ዋሉ፡፡ ወደ ምሽት ገበያ ሲፈታ አንዲት ቆንጆ ዐይኗን ጣለችበት፡፡ ከጠቢባኑ ልጅ አንዷ ናት፡፡ ከጠቢባን መካከል ሽጋዋ ጉብል ነበረች፡፡ ከተዋነይ ዐይን ላይ ዐይኗን ጥላ በፍቅር ጭምር መታችው፡፡ ጠቢብ አድርጌ ባል ይሆነኛል ብላ በፍሥሓ ተቀብላ ወደስዉሩ ዓለም ይዛው ከተፍ አለች፡፡ ወደዚህ አምጥታ በዚህ ውስጥ ያለውን ምሉእ ጥበብ አወረሰችው፡፡ የሞት መግቻውን ጭምር አስጨበጠችው፡፡ ተምሮ እንደ ፈጸመ ጋብቻውን ሠረዘ፡፡ ወደ ጠብ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው ቀለሙ፡፡

"እንዴት ጋብቻውን ሠረዘ? ፍቅሩ ለቀቀው ወይስ ጠቡን ምን አመጣው?" አለ ታሪኩ፡፡

"እረ ወዲያልኝ ወንድሜ! ተዋነይ ወደገሀዱ ዓለም ተመልሶ ቅኔ ማስተማር እንደሚፈልግ ሲናገር ቆንጆዋ በጥላቻ ጠመደችው፡፡ ሠርጉ ከተደገሰ በኋላ ጋብቻው ሲሰርዝ ደሟ





ፈላ፡፡ እሱም ቢሆን ዝም አላለም፡፡ በፍጥነት ከጠቢባኑ ዓለም ሊወጣ ወደደ፡፡ ነገር ግን ቢሞክር ሳይችል ቀረ፡፡" ቀለሙ ተፈሪ ማዶ ማዶውን እየቃኙ የታሪኩን ጭራ ይዘው ገሰገሱ፡፡

"እንደሌሎች ወንዶች ልበ ቢስ አደረገችው ወይስ?" አለ ታሪኩ ደንግጦ፡፡ ነገም በራሱ የሚደርስበት መስሎት፡፡

"የለም! የለም! ልበ ቢስ አላደረገችውም፡፡ ወደመኻል ሀገር ሂጄ ቅኔ ማስተማር እፈልጋለሁ ብሎ ከስዉሩ ዓለም ሊወጣ ሲል ግን በሩን ከረቸመችበት፡፡ የሄድሁ እየመሰለው ጫካውን ሲዞር ውሎ ማታ ቤቷ እየተመለሰ ይገባ ጀመር፡፡" ብለው ቂቂቂ አሉ፡፡

"ከዚያስ?" "ቅኔ ቤት ሳለ በሚያውቀው ጥበብ ራሱን ወደአይጥነት ለወጠ፡፡ ድመት ሆና ጠበቀቸው፡፡ ወደ ጫጬት ለወጠ፡፡ ጭልፊት ስትሆን አፍታ አልፈጀባትም፡፡ በዚህ ጊዜ "ምልዋጥ" የሚባለውን ጥበብ መነነው፡፡ ቅኔ ቤት ሳለ የሚያውቀው ጥበብ ይህ ብቻ ነበር፡፡ ቢፈትሸው ከጠቢባኑ ዓለም ለመውጣት ሳያግዘው ቀረ፡፡ ምልዋጥ ነክ የሆኑ ከርታሶችን ከዚሁ ጫካ አንድዶ ሞቃቸው፡፡ ሲሞቃቸው ለአምሮው ንጹሕ ሰሌዳ ሆነለት፡፡ በዚህ ንጹሕ ሰሌዳ የተፈጥሮ ጥበብን መሳል ፈለገ፡፡ በዚህ ጊዜ አዲስ መላ መጣለት፡፡ አባ መላ ተዋነይ የምልዋጥን ጥበብ ንቆ

የመናውን ቁራሽ ሲጋግር ትኂን ጨመረበት። እንጀራውን ከምጣዱ ላይ ጣል ሲያደርገው ቤቱ ትኂን ትኂን ሸተተ። የመናው ቁራሽ ከምጣዱ ሲወጣ ሲቀነበልባሉ ተዋነይ መናውን ቅርጥፍ አድርጎ በላው። በዚህ ጊዜ ከሁለት ነገር ነጻ ወጣ። እንዳይሞት የመናውን ቁራሽ ተመግቧል። ሴቷ እንዳትይዘው የትኂን ቅርጽ ይዟል። ትኂን ከሆነ በኂላ ነገር ተለወጠ። ተዋነይ ትኂን መስሎ ከስዉሩ ዓለም መሰስ ብሉ ሲወጣ ጊዜው ደረሰ። ባንድ ማለዳ ሴቷ አጥብቃ ስትከታተለው ከአጠገቧ ትኂን ሆነ። ድምፁን እልም አድርጎ ሁኔታዋን ይከታተላት ጀመር። እንደቀደመው የተለወጠ መስሏት ወደድመትነት ተለወጠች። ተዋነይ ወደዐይጥነት አልተለወጠም። ወደ ጭልፊት ተለወጠች። ጫጩት አልነበረም። ወደ ውሻነት ተለወጠች። ተዋነይ ሰይጣን ሲሆን አልቻለም። እሷ ሆዬ! ለውሻ ከሰይጣን ጀምሮ የሚሰወረው ነገር የለም ሲባል ሰምታ ነበር። ተዋነይ ግን ወደ ሰይጣንነት አልተለወጠም። ወደውሻነት ከተለወጠች በኂላም ተዋነይን ማግኘት አልቻለችም።" ካሉ በኂላ ትረካቸውን ገትተው።

"እንግዲህ ቅኔ ቤት ሳለን ምርጥ ጥበብ መስሎ የሚታየን ምልዋጥ የሚባለው አስማታዊ ጥበብ ነበር። እኔን ጨምሮ እልፍ የቅኔ ሊቆች ምልዋጥ ፍለጋ ስንት አቀበት ወጥተናል። ስንት ወንዝ አቋርጠናል። ምልዋጥ ግን ተራ ጥበብ መሆኑ





በዚህ ጊዜ ታውቋል። ለምን ቢባል? ተዋነይ የተጠቀመው መናውን እንጂ ምልዋጡን አይደለም። ምልዋጥ በልበ-ቢሶች ዘንድ ፍቱን ጥበብ ቢመስልም ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ተራ ነገር ነው። ሰው በአስማት ሲለወጥ አእምሮው ጭምር በቅጽበት ይለወጣል። "ምልዋጥ" ተፈጥሮንም ያዛባል።" ብለው ምልዋጥ የሚባለውን የአስማት ነገር አንክሳክሰው ጣሉት።

"ተዋነይ ግን የሠራው ነገር ግን ጉድ ነበር። ትኂኑን ከመናው ጋር ጋግሮ መናውን ሲቀምሰው ትኂን ሆኖ ወደመኻል ሀገር ተመለሰ። ይህ ክፋት የለውም። ከአስማትም ጋር ቁርኝት የለውም። ጠቢባኑ ከመናው መሳተፍ የለባችሁም የሚሉት እንደተዋነይ ትኂን ሁናችሁ ከዚህ ዓለም ወደመኻል ሀገር ሄዳችሁ ምሥጢር ታወጣላችሁ፤ ሀገራችን በባዕዳን ወራሪዎች ትመዘበራለች ብለው ነው። ይህ ደግሞ ክፋት የለውም። ምሥጢር ለመጠበቅ ነው።" ዝም ሲሉ

"እኛ እንኳን በዚህ አንጠረጠርም ነበር። ዝም ብለው ቢያስገቡን ምን አለበት?።" አለ ገሞራው የሚለው አጥቶ

"እናንተ ያንን ሳትሠሩ ትችላላችሁ። ደቂቀ ተዋነይ ግን ከዚህ ዓለም እንዳትገቡ የከለከሉት ለዚህ ነው። ተዋነይን አብነት



Scanned with CamScanner

አድርጋችሁ አብነቱን ይዛችሁ ትኮበልላችሁ ብለው ሰግተዋል።

እኔ ግን መናውን ትቀምሱ ዘንድ እየተከራከርሁላችሁ ነው። አንድ ቀን ከመናው ትቀምሱ ይሆናል። ለማንኛውም እግዚአብሔር ይርዳችሁ።" ብለው በተስፋ ሞኋቸው። ተረጋግተው አደሩ።





# ፳፫

ጦማረ ተከስተ

ወደመጨረሻው ጉባኤ ግድም የተከሰተ ደብዳቤ ከተወሸቀበት ተፈልጎ እንዲህ ተነበበ። አንባቢው ዐራት ዐይናው ነበሩ።

"ቀዳማይ ሆይ! ጃንሆይ ቀዳማይ! ጃማይካ ሲደርሱ ዝናም በዝናም እንደሆኑ ከዚህ ሀገር ሲወራ ሲነቦግ ሰነበተ። ግርማይነትዎ ሆይ! ቀዳማዊትዎ የጥበብ ሊቃውንትን በመውደድ ጥሩ ስም አለዎት። ይህ ደግሞ ግርማይትዎን ግርማ ሞገስ እንዳጎናጸፈዎ ከልብ አምናለሁ። እኔም ከጠቢባኑ ዓለም ወደ ቤተ መንግሥት የመጣሁት መፍቀሬ ጠቢባን እንደሆኑ ተረድቼ ነበር። ነገር ግን ቤተ መንግሥቱን የሞሉት የስም ሊቃውንት ለኢትዮጵያም ሆነ ለግርማነትዎ ክብር የሚመጥኑ አይመስለኝም። መኳንንቱም ይብሳሉ። ይልቁም ሴቶች ለጃንሆይነትዎ የተለየ የአክብሮት ፍቅር አላቸው። የእርስዎን እግር አጥበው ከግርማይትዎ አንድ አቡነ ዘበሰማያት እንደሚፈልጉ ይሰማኛል። ከሴቶች ልብ ውስጥ ያሉ ርስዎ ብቻ ነዎት። ይወድድዎታል። መውደዱ ደግሞ አክብሮት የተጨመረበት ነው። አዳም ሔዋንን፣ ዳዊት

አቤግያን፣ በወደዱበት መውደድ አይደለም፡፡ ይህንን በቆይታዬ ተረድቻዋለሁ፡፡ የቤተ መንግሥት አጭር ቆይታዬ ይህንን ነግሮኛል፡፡ ለካ ስሜን አላስቀደምሁም! ይኸንን የስንብት ደብዳቤ የምጽፍልዎ የስዉሩ ዓለም ሰው ተከስተ ዝናቡ ነኝ፡፡ የስንብት ደብዳቤዬን የምጽፍለዎ ደግሞ ያው ወደ ጠቢባን ዓለም ለመመለስ ውሳኔ ላይ ስለደረስሁ ነው፡፡ ከግርማዊነትዎ ጋር በነበረኝ አጭር ቆይታ የቀኑ ሰዎች ምንኛ እንደ ጠሉኝ ስመለከት ቤተ መንግሥቱን መመነኔ ነው፡፡ ግርማይ ሆይ! ድሮም እኔ ምስኪን የቆሎ ተማሪ ነበርሁ፡፡ ወደ ፊት መንግሥተ ሰማይ መግባት እንጂ በመንግሥትዎ በኩል የሥልጣን ተምኔት የለኝም፡፡ የዕለት ራቴ ሳይቀር ከቤተ መንግሥት በኋላ ከሚቀቀለው በድስት ከሚንተከተከው ምግብ የተለየ ነው፡፡ ጃንሆይ! እንጀራ መብላት ካቆምሁ ዓመታት አልፈውኛል፡፡ ከጠቢባን ዓለም በወረስሁት የኅብስተ መና ምሥጢር እየተጠቀምሁ ትኩስ እንጀራ በአፌ ዙሮ አያውቅም፡፡ ስሞኑን ወደቤተ መንግሥት ስመጣ እንኳን ከቤተ መንግሥቱ ፍትፍት ከቤተ መንግሥት ጠጅ አልቀመስሁም፡፡ ይህ ሁሉ በሆነበት ቤተ መንግሥት ለመሰንበት ጥሩ ስሜት አልተሰማኝም፡፡ በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ ቀለብ የሚሰፈርላቸው በክፉ ዓይን እየተመለከቱ ሲያሳቅቁኝ ጊዜ ወደ ጠቢባኑ ዓለም ተመልሻለሁ፡፡ ወደ ደቂቀ





ተዋነይ፡፡ ሌላ ጊዜ ወደ ቤተ መንንግሥት መጥቼ እጠይቅዎታለሁ፡፡ ለጊዜው ግን ወደ ጠቢባኑ ዓለም ተመልሻለሁ፡፡ የግርማዊነትዎ ክብርና ፍቅር አይለየኝ...፡፡"

ደብዳቤው ተነብቦ ሲፈጸም ዐራት ዐይናው ቀሪውን በቃላቸው ማብራራት ቀጠሉ፡፡ ቃል በቃል እንደሰሙት አድርገው ነበር ያብራሩት፡፡

"ውስጠ አዋቂዎች ፍቅር እስከ መቃብር የተከስተ ታሪክ ነው ይላሉ፡፡ የልብ ወለዱ ደራሲ አዲስ ዓለማየሁ ይባላሉ፡፡ ልብ አንጠልጣይ ታሪክ ቀመስ ልብ ወልድ ጽፈዋል፡፡ ልብ ወለዱን እኔም አንብቤዋለሁ፡፡ ርእሱ ፍቅር እስከ መቃብር ነው፡፡ መጽሐፉን ሀገር ያውቀዋል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ይህንን ውስጠ ወይራ ያውቁ ነበር፡፡ ፍቅር እስከ መቃብር በሚለው የድርሰት መጽሐፋቸው በዛብህ ሲሉ ስሙን ለውጠው ታሪኩን የከተቡለት ባለ ታሪክ ተከስተ ነው፡፡ በድርሰቱ እንደተገለጠው ተከስተ የቅኔ ተማሪ ነበር፡፡ ጃንሆይ በገጸ ባሕርዩ ፊት አውራሪ መሸሻ ተብለዋል፡፡ ልጃቸው በሰብለ ወንጌል ተመስላለች፡፡ ሰብለ ወንጌል ከበዛብህ ጋር ፍቅር ይዟታል፡፡ ፊት አውራሪ ግን በዛብህ ከነ ፋሲል ከነምትዋብ ጋር የንግሥና ደም ስለሌለው የሰብለ ወንጌል መምህር እንጂ ፍቅረኛ መሆን እንደማይችል ያምናሉ፡፡ ተማሪውንም የሰው ልክ የሚያውቅ የነገሥታቱን ምንጣፍ

የማይረግጥ የጨዋ ልጅ ሲሉ በመኪንንቱ ፊት ያወድሱታል። ያ በዛብህ በገሀዱ ዓለም ያለው ተከስተ ነበር። ሰብለ ወንጌል ደግሞ ከተከስተ የተገኘችዋ ሀገራዊ ጥበብ ናት። በዛብህ ለሰብለ ወንጌል ፍቅር መሞቱ ተከስተ ለጥበብ መሞቱን ያመለክታል። በመጽሐፉ እንደ ተገለጠው ሰብለ ስታፈቅረው አባቷ ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ይቀራሉ። በዚህ ተለያይተው በዛብህ ወደ አዲሳባ ይሄዳል። ሰብለ ወንጌልም ያለእሱ መኖር እምቢ ይላታል። በዛብህም ከአዲሳባ ገብቶ ያለሰብለ ወንጌል መኖር ተሣነው። እሱ ከአዲሳባ ወደ ጎጃም፣ እሷ ከዲማ ወደአዲሳባ በመሄድ ላይ እያሉ በዛብህ ዐባይ ሸለቆ ውስጥ በሽፍቶች ተቀጥቅጦ አገኙት። ደግፋ ደጋግፋ ብታስታምመውም ሊሻለው አልቻለም። ሞተ ተቀበረ። ከሞተ በኋላ ሰብለ ወንጌል ወደ ሀገሯ አልተመለሰችም። በዛብህ ከተቀበረበት ደብር መንኵሳ ፍሬ ግብር እየፈጨች ማይ እየቀዳች ኑራ አብራው ትሞታለች። ከጊዜ በኋላ ደግሞ ጉዱ ካሣ ይደገማል። ሦስቱም የጥበብ ሰዎች በአንድ አጸድ ውስጥ ወድቀው መቅረታቸው ተከስተ ከጠቢባኑ ዓለም ከወጣ በኋላ አለመመለሱን ያስረዳል። ከዚህ ላይ ልብ በሉ። ወደ ጠቢባኑ ዓለም ያልተመለሰው ተከስተ ብቻ አይደለም። የተከስተ ድንቅ ጥበብ ጭምር ናት። በበዛብህ ልብ ውስጥ ሰብለ ወንጌል አለች። ከዚያ ፍቅር። በምሳሌ ሲገለጽ ቀድም





ተከተሉን ተመለከቱ። ተከስተ በበዛብህ፣ ሰብለ ወንጌል በጥበብ ይመሰላሉ። ከድርሰቱ ወደ ገሀዱ ዓለም እንምጣ !" ብለው በምሳሌ መግለጥ ጀመሩ።

"ልብ ወልድ የገሀዱ ዓለም ነጸብራቅ ነው ይባላል። ከዚህ ብሂል የተነሣ በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ የተካተቱ ፍሬ ፍሬ ሰዎች የገሀዱ ዓለም ነጸብራቆች ናቸው። በልብ ወለዱ ዓለም በዛብህ፣ ሰብለ ወንጌል፣ ጉዱ ካሣ ሲሆኑ ተከስተ በበዛብህ፣ ሰብለ ወንጌል በጥበብ ይመሰላሉ።

በአንድ መቃብር እንደተቀበሩ ተከስተም ሦስት ነገር እንደያዘ ተቀብሯል። እነሱን ታውቋቸዋላችሁ። አልናገርም።" ብሎ ወሽከትሁ መሰለኝ ብለው ሀገራዊውን ምሥጢር ገቱ። ወሽከትሁ እንዳሉ ግን አልወሸከቱም።

"ደራሲው ተከስተን በበዛብህ መመሰላቸው በእኔም በኩል ትክክል ምሳሌ ነው ባይ ነኝ። መከራው በዝቶበታል። ዱላ ወርዶበታል። ንጉሡም እንዲህ ዐይነት መጽሐፍ በዘመናቸው ሲጻፍ ደንግጠው እንደነበር ጥርጥር የለውም። ደራሲው ግን ላብ-ወልድ ነው ሲሉ አስተባበሉ። ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ሆኖ ታለፈ። ደራሲው ምሥጢር ሳያወጡ ከጃንሆይ ጋር በምሥጢር ቃለ መሐላ እንደ ፈጠሙ ይወራል። የመጽሐፉ

ጭብጥ ግን የተከሰተ የጥበብ ታሪክ ነው።" ብለው አፍታ ከወሰዱ በኋላ ጨመሩበት።

"ማመን አልቻልሁም። እስከ ዛሬ ከታሪክም አላነብሁም። በጃንሆይ ሕይወት ላይ የሚያጠነጥን ብዙ ታሪክ አንብቤአለሁ።" አሉ ሖረ።

"ከቤተ መንግሥት የተደረገውን ምሉዕ ምሥጢር ማወቅ አይቻልም። ጥበብ ቀመሱ ታሪክ ደግሞ ሊጻፍም አይችልም። ወደ ቤተ መንግሥት ለመሄድ በተነሣ ጊዜ ከሲራራ ነጋዴዎች ጋር ዐባይን እንደ ተሻገረ የቅኔ ቤት ጓደኞቹ ያውቃሉ። እኒህም የዋድላው ሊቅ ከበደ፣ የአንኮበሩ ዘርአ ዳዊት፣ የጎጃሙ እቡይ ካሣ ናቸው። ሁሉም የቅኔ ቤት ጓደኞች ነበሩ። ወደ ቤተመንግሥት ሲሄድ ዐባይን በወሰካ አሻግረውታል። ከዚያም ከሲራራ ነጋዴዎች ጋር ደንበውታል፡ ፡ ከዚያ በኋላ ጉዞው ግልጽ ነበር። ቀጥታ ቤተ መንግሥት ገባ። ጓደኞቹ እንዳሉት እንቅፋቱ የጀመረው ግን ዐባይን ሲሻገር ጀምሮ ነበር። ያ ጊዜ ዐባይን የሚያሻግር ሰባራ ድልድይ አልነበረም። ሁሉም በእግር ነበር የሚሻገረው። ተከስተም ዐባይን ሲሻገር ጓደኞችን ጨምሮ ቀጭን አዞ ልትውጣቸው ስትል በተአምር መተርፋቸው በስፋት ይወራል። ከአዞ ጥርስ እንደምንም አምልጠው ዐባይን





ከተሻገሩ በኋላ ሦስቱ ጓደኞቹ ከዚያው ዐባይ ሸለቆ ውስጥ ሰንበቱ። ተከስተ ወደ ቤተ መንግሥት ገሰገሰ። ጓደኞቹ በዐባይ ሸለቆ ውስጥ ካሉ ባላገሮች ተጠግተው ለአያሌ ቀናት ጠበቁት። ጥበቃቸው በተስፋ የተመላ ነበር። ሲመለስ ቃሉን ይጠብቃል የሚል አጉል ተስፋ ሰንቀው ሲነሆልሉ ሰነበቱ።" አሉ ዐራት ዐይናው።

"ምን ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር?" አሉ ጠቢቡ ሖረ ጣልቃ ገብተው።

"የኤልያስ አምላክ በሰላም ወደ ጠቢባኑ ዓለም ከመለሰው አንዲት ቃል ገብቶላቸው ነበር። እነሱ ከቤተ መንግሥት ወደ ጠቢባኑ ሲመለስ ከዐባይ ወንዝ ጠብቀው ዐባይን በወሰካ ሊያሻግሩት እሱ ከዐባይ ወንዝ ዳር ለዳር ወቅት ጠብቃ የምትበቅለዋን የሕይወት ዛፍ ሊያሳያቸው ቃል ነበራቸው። በዚህ ውል መሠረት ክርታተው ተከስተ ከቤተ መንግሥት ወደ ጠቢባኑ ዓለም እስኪመለስ ለአያሌ ቀናት ከዐባይ ወንዝ ዳር ሰፍረው ሰነበቱ። ቢጠብቁት ቢጠብቁት ቀረ። ተስፋ ቆርጠው ወደ ቅኔ ቤት ሊመለሱ ሲሉ አንድ የቅኔ ተማሪ በሽፍቶች ተቀጥቅጦ ሞተ የሚል ወሬ ሰሙ። ወደጎሐ ጽዮን አፋፍ ገሰገሱ። ሲደርሱ ከእግር እስከራሱ ከጸጉሩ እስተጥፍሩ በደም ተነክሯል። እስትንፋሱ ተዳክሟል። የልብ ምቱ

ቁሟል፡፡ ከደረቱ ላይ ብቻ ያተኩሳል፡፡ ከወገቡ በታች በድን፣ ከወገቡ ራስጌ ሕያው ሆኖ አገኙሁት፡፡

ያ ሊቅ ተከስተ ነበር፡፡ ይሻለዋል ብለው ቢጠብቁ ቢንቀራጠጡ ለውጥ አጡ፡፡ ብዕር አንሥተው ሰጡት፡፡ መክተብ ተሣነው፡፡ ተስፋ ቆርጠው ነፍሱ ከሥጋ እስክትለይ እግር ከራስጌ ሆነው የሞቱን ቀን መጠበቅ ያዙ፡፡ ምንም ተስፋ አልነበረም፡፡ የጓደኞቹን ዐይን በዐይኑ እያየ አመለጠ፡፡ አንሥተው ጎሐ ጽዮን ቀበሩት፡፡ ከቀብሩ በኋላ የተነሣው ምሥጢር ግን አሁን ድረስ አጨቃጫቂ ነው፡፡ የተከስተ አጫቃጫቂው ከእኛ ደረሰ፡፡ ጭቅጭቁ ከዚህ ላይ አያበቃም፡፡ ወደፊትም መነሣቱ አይቀርም፡፡" ብለው እንባ ቀደማቸው፡፡ ሲቃ ተናነቃቸው፡፡ ትኩስ እንባ አፍስሰው ስሜታቸው ጋብ ሲሉ ተረጋግተው ቀጠሉ፡፡

"የተገደለበት ስፍራ በራሱ አከራካሪ ነበር፡፡ ከቤተ መንግሥት ከወጣ በኋላ መርካቶ ላይ ቀጥቅጠው ጎሐ ጽዮን ድረስ አምጥተው ጣሉት የሚሉ አሉ፡፡ ከፊሎች ግን ከቤተ መንግሥት ወደ ጠቢባኑ ዓለም ሲመለስ መኪንንቱ ገዳይ ልከው ዐባይ ሸለቆ ሲደርስ አስገደሉት ይላሉ፡፡ የእኔ ጥያቄ ይህ አይደለም፡፡ ደቀኛው የሞት መግቻውን ስለነጠቀት





ተገደለ ባይ ነኝ፡፡ የጠቢቡን ሞት ካስረዳሁ ፍርዱን ለጠቢባኑ እተወዋለሁ፡፡" ብለው ወደጠቢባኑ እጅ ነሥተው ተቀመጡ፡፡

የመጀመሪያው ፍትሕ ሰጪ ወይራው ነበሩ፡፡

"ተከስተ የተቀሰፈው በራሱ ነው፡፡ በስዉሩ ዓለም ተረጋግቶ መኖር ሲችል እንደ ፊንጣ በርሮ ቤተ መንግሥት ገባ፡፡ መግባቱ ሳያንስ የሀገራችን ሊቃውንት ጠምጣሚ ብቻ እያለ ሲዘልፋቸው ሰነበተ፡፡ ተነደው በጥላወጊ ገረደሉት፡፡ ጎሐ ጽዮን እንደተቀበረ ሰምንተን አሰቅስን፡፡ በዚህ ጊዜ ራሳቸው ደቀኛው እንባቸው እንደ ጢስ ዐባይ ፏፏቴ ሲንፏፏ ሰነበተ፡፡ ከሁሉም ኀዘኑ የጎዳቸው ደቀኛውን ነበር፡፡ በወቅቱ ከስዉሩ ዓለም ወጥቼ እሞታለሁ ብለው እኔ በጭንቅ ገልግዬ ከሞት አዳንኋቸው፡፡ ያን ጊዜ ሂደው ቢሆን ደቀኛውም ተከስተ ነበሩ፡፡ ጠቅለል ሲል ደቀኛው በሞቱ በኩል የሉበትም፡፡" ሲሉ ደቀኛው ገጻቸው ፈካ፡፡ ፍትሕ በእግሯ ስትሽከረከር አይተው ለቅለቅ ብለው አለቀሱ፡፡ ወይራው ግን ቀጠሉ፡፡

"ደቀኛው እንዲህ ሸንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩት የሀገርን ምሥጢር ለመጠበቅ ነው፡፡ አሁንም እኒህ የአብነት ተማሪዎች ወደ ውስጥ መግባት የለባቸውም ባይ ነኝ፡፡" ብለው ሲፈጽሙ ጠቢባኑ እጃቸውን አውጥተው አጨበጨቡላቸው፡፡ ደቀኛው ረትተው ዐራት ዐይናው



Scanned with CamScanner

ተረትተው ጉባኤው ሲፈታ ዐራት ዐይናው ገሞራንና ታሪኩን ለማስናበት ወስነው ወደ ዐለቱ ሲመለሱ ገሞራው ታሞ ተጋድሟል፡፡ የጥርሱ ነገር የወግ አይደለም፡፡ ጭንቅላቱ ድረስ ወጥቶ እየሰቀሰቀው ነበር፡፡





## ፳፮

የሞት ቀን

ዐራት ዐይናው ከዘግባው ወደ ሁለቱ ሲቆች እንደ ደረሱ ተነፈሱ፡፡

"ላልመጣ የሰነበትሁት ጉባኤውን እየመራሁ ነበር፡፡ ዛሬ ተርትቼ ተመልስሁ፡፡ ክርክሩ ደግ ቀጥሎ ሰንብቶ ነበር፡፡ ዱሩ ምን ይሆናል? ጠቢባኑ ወደ ስዉሩ ዓለም እንድትገቡ አልፈቀዱም፡፡ እኔና ሖረ ሽንጣችን ገትረን ስንከራከር ሰነበትን፡፡ ዛሬ ግን በጠቢባኑ ፊት ተረታን፡፡ አሁን የመጣሁት ላሰናብታችሁ ነው፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው ቀለሙ እየተከዙ፡፡

"እኛም ከስዉሩ ዓለም ገብተን መናውን ቀምሰን ከሞት የማንድን ከሆነ ወደ ሀገራችን ለመመለስ ወስነናል፡፡" አለ ገሞራው በትሕትና፡፡

"እንዴት?" አሉ ቀለሙ ተፈሪ ደንግጠው፡፡

"እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ጥርሴን ያመኛል፡፡ አሁን ደግሞ ሕማሙ እየባሰብኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ምሥጢር እየነገረኝ ነው፡፡ የጸደይን ጨረቃ እየፈራኋት ነው፡፡ ከጸደይ

## ፳፪

ከሰይጣን ጋር ራት

ዐራት ዐይናውን ከሸኙ በኋላ ሁሉቱም ስለ መናው በየፊናቸው ሲያሰላስሉ የገሞራው ጥርስ ቁርጥማት ጭልጥ አለ። የሞት ተነሣበት። ገሞራው ወደ ሌላ ሐሳብ ጭልጥ አለ። የሞት ጊዜው እንደደረሰ እያሰላሰለ ከታሪኩ ፊት ለፊት ከዐለቱ ላይ ጋደም ብሎ ጥርሱን ይጎረጉራል። በዚህ ሳምንት ደግሞ የጥርሱ ነገር አንገብግቦታል። በግራ ጉንጩ በኩል ጥርስ ቁርጥማት ያላምጠዋል። የሕማሙ ስሜት በቀኝ በኩል ጭምር ይሰማዋል። ድዱ ትኩስ ደም ጎርሷል። ከጥርሱ ውስጥ የተሰገሰገውን የአበው ጎመን የሚባለውን ቅጠል ከተቦረበረ ጥርሱ ለማላቀቅ በቀጭን ለበቅ ጥርሱን ጎርጉሮ ይባስ አሳምሞታል። በዚያ ላይ ብርዱ ሆዱን እየነፋው ሩጥ ሩጥ እያለው ነው። ከመናው ቀምሶ ከሞት ካልተገላገለ በቀር ረጅም እድሜም ያለው አይመስልም። በጥርሱ በኩል የሚገዘግዘው ደዌ ለሞት የሚያደርስ በሽታ እየሆነ መጥቷል፡ ፡ ከዚህ በፊት በዚሁ የጥርስ ቁርጥማት መሰል በሽታ ትልቅ ወንድሙን አጥቷል። ኋላም ውድ እኅቱን ቀብሯል።

ልጅ እያለም እናቱ በዚሁ ደዌ ከዚህ ዓለም እንደተለየች ዜና ሞቷን ተረድቷል። ራሱ ገሞራውን እያጠባች እያለች ነበር በጥርስ ቁርጥማት መሰል ደዌ መቃብር የወረደችው። በዚህ ሕማም የተነሣ እንደ ማውታ ሆኖ እንዳደገ ከገሞራው በቀር የሚያውቅለት የለም። እናቱ፣ እኅቱ፣ ወንድሙ የሞትን ጽዋ እንደጠጡ በተራ ጨልጠውታል። አሁን ደግሞ ተራው የገሞራው ነው። በነገሞራው ቤት ሞት በተራ ነው። ዳሩ ግን የሞት ተራው ከመድረሱ በፊት እንደ ተዋነይ ወደስዉሩ ዓለም ገብቶ መልአከ ሞትን ገዝቶ መኖር ፈልጓል። ለዚህ ነበር ቶሎ መናውን መቅመስ መሻቱ። መመኘቱ! መጎምጀቱ! መሰሰቱ! ከዐራት ዐይናው እግር ሥር መሰንበቱ! ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ መምሸት አይቀርምና መሸ። ብርዱን ተከትሎ የመጣው የጥርስ ቁርጥማት የራስ ምታት አስከትሎበት ሲወዛወዝ አምሽቶ አንድ አስጨናቂ ሐሳብ ብልጭ አለበት። ወደ ታሪኩ ዘወር ብሎ መቁለጭለጭ ጀመረ። ከዚያም ወደአለቱ ጠጋ ብሎ .

"የጸደይ ጨረቃ ሲያልቅ እየተገባደደ ነው። ሰኔ መጨረሻ ገድም ያከትማል። አሁን በሰኔ ወር ከመናው ካልቀመስሁ ወደሀገሬ እመለሳለሁ።" አለ ገሞራው።

"ለምን? በስዉሩ ዓለም ልንኖር አይደል እንዴ ሀገር አቋርጠን ወንዝ ተሻግረን የመጣነው? የምን ሰኔ ነው? ውሳኔውን መጠበቅ አለብን::" አለ ታሪኩ::

"ጥርስ ቁርጥማቱ እየባሰብኝ ነው:: ይህ ደግሞ አንድ ምሥጢር እየነገረኝ ነው::" ገሞራው ቡዝዝ ፍዝዝ እንዳለ እንባ በዐይኑ ተኳለ:: ራሱ በተናገረው ቃል እንባው ተናነቀው:: ታሪኩ ግራ ገብቶት በአትኩሮት ተመለከተው::

"ማርያምን! መመለስ ከቻልሁ እመለሳለሁ:: በእርግጥ በዚህ እኩይ ዘመን ተመልሼ ወደቅኜ ቤቴ መድረስ ቀላል ነገር አይደለም:: ኢትዮጵያ ምስቅልቅሉ ወጥቷል:: ሞት በየቁጥቋጦው ተወሽቋል:: ብጥብጡ ቀዝቀዝ ካለ ወደቅኜ ቤቴ ተመልሼ በዚያ መቀበር እፈልጋለሁ:: በየኔታ መወድስ ግብአተ መሬቴ ይፈጸማል:: እንደ ኄርማ ያለመወድስ መቀበር አልፈልግም::" አለ ገሞራው::

"መቃብር! እረ በስመ አብ በል! የምን ቀብር ነው የምታወራው?" አለ ታሪኩ ግራ ገብቶት እያማተበ::

"መልአከ ሞትን አውግዘን እስከፈለግነው በሕይወት ለመኖር ወስነን መጥተን ሞትን ትጠራለህ?" ታሪኩ እየተርበተበ ተመለከተው::





ታሪኩ በገሞራው ንግግር ቢርበተበት ይገባዋል:: ለምን ቢሉ? ገሞራው የዋዛ ሰው አይደለም:: የሚሞትበትን ቀን ለይቶ ያውቃል ተብሎ ይገመታል:: በከፊል የቀመር ሊቅ እስከሆነ ድረስ ያ ነገር ያቅተዋል ተብሎ አይገመትም:: እሱም ቢሆን በቀልድ መልኩ ተናግሮት ያውቃል:: ሞትን በሚፈሩ ሰዎች ጭምር ሲስቅ ነበር:: ወደ ስዉሩ ዓለም ለመግባት መፈለጉም ለዚህ ይመስላል:: ጥቂት እድሜ ኑሮት አንዳንድ ነገር መሥራት ይፈልጋል:: የተዋነይ ዓለም ሰዎች ደግሞ መልአከ ሞትን የመገዘት ኀይል በእጃቸው እንደሆነ ከልጅነቱ ሲወራ ሰምቷል:: ይህንን የመሰለ ውድ ጥበብ ባለባት ሀገር እየኖረ እናቱ በሞተችበት ሞት ሊሞት አይፈልግም:: የወንድሙና የእኅቱ ተከታይ ሆኖ የሙታን አጃቢ ሊሆን? እንዴት ብሎ? ገሞራው ሁሉን መመርመር ቢወድም በሞት በኩል ያለው ምርምር ግን ቀላል ነው:: የራሱን የሞት ቀን ለይቶ ለማወቅ እምብዛም ድፍረቱ የለውም:: ጀምሮ ይተወዋል:: "በፈጣሪ ሥራ እኔ ፍጡሩ መግባት የለብኝም:: ይህ በአበው ዘንድ የተወገዘ ነው" ሲል ለራሱ ይናገራል:: በእሱ በኩል ያለው እሱ ብቻ ነው:: በእርግጥ የሞትን ምሥጢር ቢፈልግ በቀላሉ ማወቅ ይችል ነበር:: ከፍልስፍናው ይልቅ መንፈሳዊነት ስለሚበልጥበት ወደዚህ ምሥጢር ዘው ብሎ ገብቶ ተፈላስፎ አያውቅም እንጂ:: ወደዚህ ሐሳብ ለመግባት በቅጽበት ወስኖ

በቅጽበት ያፈርሰዋል፡፡ ለፈጣሪ ይተወዋል፡፡ "በፈጣሪ ሥራ መግባት አይፈልግም፡፡ የእኔ ሥራ በተፈጥሮ ላይ መመራመር ብቻ ነው፡፡ መግደል ማዳን የጌታ ሥራ ነው ሲል" ለብቻው ይኩተመተማል፡፡ በዚያ ላይ ወደ ስዉሩ ዓለም ከገባሁ ምሥጢሩ ከዚሁ ይጠብቀኛል ሲል ቸላ ይለዋል፡፡ ዛሬ ግን ስለጥርሱ ሕማም ሲያሰላስል ቆይቶ የወንድሙ እጣ ፈንታ ትዝ አለው፡፡ በጳደይ ወር የጀመረው የጥርስ ሕማም ከዚች ዓለም እንዳሰናብተው ትዝታው መጣበት፡፡ ገሞራው ቀጠለ፡፡

"በዚች ዛፍ ሥር የምቆየው እስከ ጳደይ ወር መጨረሻ ብቻ ነው፡፡ ከጳደይ ወር በኋላ ወደቅኔ ቤቱ እመለሳለሁ፡፡ የመልአከ ሞትን ጽዋ ቅኔ ቤት እጨልጠዋለሁ፡፡ ይህ መና በራሱ ከሰይጣን ዓለም የሚመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያ ላይ የመና ቁራሽ ነገር ለዓለም ጠበብት ግልጽ ጥበብ አይደለም፡፡ ጥንቁልና ሊሆንም ይችላል፡፡ በዚያ ላይ መናው ከሰይጣን አለመምጣቱን ማረጋገጫ የለንም፡፡" አለ ገሞራው

"ተው እንጂ ገሞራው! ዛሬ ትክክል አይደለህም፡፡ ድሮውኑ ወደዚህ ዓለም እንድመጣ ያነሣሣኸኝ አንተ ነበርህ፡፡ ጌርማ መንገድ የቀረው የስዉሩን ዓለም ምሥጢር ለማጥናት እየናፈቀ ሳለ ነበር፡፡ እኛ ግን እስከመጨረሻው ውሳኔውን





መጠበቅ አለብን፡፡ ከሰይጣን ሊሆን ይችላል በምትለው ውስጥ የእኔም ጥርጣሬ ነበር፡፡ አሁን ግን ከሰይጣን እንደማይሆን እያመንሁ መጥቻለሁ፡፡ የሰይጣንን ውትልፍ ምሥጢር ቀደም ሲል አይቸዋለሁ፡፡ መና አምጥቶ እንደማይመግብ ተረድቻለሁ፡፡ ግፋ ቢል ወደመንደር ወስዶ ቁራሽ ካለበት ሊያደርስ ይችላል፡፡" አለ ታሪኩ ሰይጣንን እያነናቀ የጠቢባኑ ውሳኔ እየጠበቀ፡፡

"እንዴት እንዴት?" ገሞራው ተፈናጥሮ ሄዶ ከአጠገቡ ቆሞ አለ፡፡ በደንብ ለመስማት ነው፡፡

"ቅኔ ቤት ሳለሁ ሰይጣን ይሁን ወይም ዛር ራት ሊመግበኝ ፈልጎ ሲያቅተው አይቸዋለሁ፡፡" አለ ታሪኩ ከሰይጣን ጋር ራት ሊበላ ከሰው እይታ የተሰወርባትን ቀን ወደኋላ ተመልሶ እያስታወሰ፡፡

"እረ ባክህ አያ! ከሰይጣን ጋር ማን አገናኘቶህ? ተዋርሰህ ነበር ልበል እንዴ?" አለ ገሞራው፡፡

"ራሱ መጥቶ ነዋ!" ሲል በጣም ከት ከት ብሎ ሳቀ፡፡ ወደኋላ ተገልብጠ ሲስቅ ገሞራው ግን ፈገግ እንኳ አላለም፡፡ ደንግጧል፡፡ ሰው ሲደነግጥ ይረበሻል እንጅ ስቆ አያውቅም፡፡



Scanned with CamScanner

“ከሰይጣን ጋር ራት ለመብላት የተሰየምሁት ቅኔ ቤት ሳለሁ ነበር። ቀኑ የፋሲካ ምሽት ነበር፤ ባንድ ፋሲካ ቀን ላይ መንደር ለመንደር ዘወር ዘወር እያልሁ በእንተ ማርያም ስል ውዬ ወደማታ ለብቻዬ ስኳትን አንድ ጥላ ዘበብ አለብኝ። ወደኋላየ ዘወር ስል ኮቴም ሆነ የሰው መዓዛ የለም። ዘወር ዘወር እያልሁ መንገዴን ቀጠልሁ። ሰዓቱ በጣም እየመሸ ሲመጣ ትክሻዬን እየከበደኝ ሄደ። ጥቂት ቆይቶ መናገር የማይችል ነገር ግን በከንፈር ጥቅሻ የሚያዝዝ መንፈስ በፊቴ ተገደገደ። ፈዝዤ ቆምሁ። የጣቱን ቀለበት አውልቆ ወደ ጣቴ ላካት። ከጣቴ ጋር ለከክ አለች። ከዚያ በኋላ የገጠመኝን ችግር ባልናገረው ይሻላል።” አለ ታሪኩ እንዴት እንደተርበተበተ እስታውሶ።

“እረ በማርያም ጨርስልኝ!። ይህን የመሰለ እኩይ ነገር ጀምረህ ማቆም የለብህም። ይልቁንም ዐራት ዐይናው እስኪመጡ ፀሐይ ወደመስኮቷ እስክትጠልቅ አውራኝ።” ገሞራው እንዲጨርስለት ጓጉቷል።

“መጨረሻው አሳዛኝ ነገር ነው። እንደቆላ ወባ መናገር ያንቀጠቅጣል። ቢቀርብህ ይሻላል።” አለ ታሪኩ ባለመፈለግ።





“የፈለገውን ያኽል ከባድ ቢሆንም መጨረሻውን ትነግረኝ ዘንድ በሊቁ በክፍለ ዮሐንስ ስም ይዠኻለሁ። የዲማው ጊዮርጊስን! ሳትነግረኝ ዛሬ ወደሌላ ምሥጢር አንሄድም። ይልቁንስ ተረጋግተህ አምጣው። ከዚያ በፊት ግን ረሐብ አድክሞኻል መሰለኝ። ምግብ ማስቀድም አለብኝ።” ፈጠን ብሉ ተነሥቶ የተልባ ማር አዘጋጅቶ አቀረበለት። ታሪኩ ያን እየዋጠ ቀጠለ።

“ልጅ እያለሁ ጀምሮ በአዲስ ዓመትም ሆነ በትንሣኤ ከወላጆቼ ጋር አክብሬ አላውቅም። ባመት ባመት ቅኔ ቤት ነው የማከብረው። የዐሥራ ዘጠኝ ዘጠና ስምንት ዓመትን ትንሣኤም ያከበርሁት ዋሸራ አካባቢ በሚገኝ ሰፈር ነበር። “እንዘ ግድም መንደር” ይባላል። ይህ እንዘ ግድም በታሪክ ድርሳንም ተጠቅሷል። በዚሁ አካባቢ የሚኖሩ ለጊዜው ስማቸውን የረሳኋቸው ሊቅ ነበሩ። በዐሥራ ዘጠኝ ሃያ ስምንት በጣሊያን ወረራ ጊዜ ጉባኤ ፈትተው ወደጦር ሜዳ ሲሄዱ እንዘ ግድም ከሚባል ስፍራ የዘረፉት ቅኔ በመዝገበ ቅኔ ተከትቧል። ቆላ ወርጄ በእንተ ማርያም ብዬ ስመጣ ከዚያ ክፉ መንፈስ ጋር ተጋጠምሁ። ግም አጋጣሚ ነበር። ቀለበቷን ከጣቴ ሰክቶ ተከተለኝ የሚል ምልክት ሰጠኝ። ከምልክት ቋንቋው በቀር ድምፅ አይወጣውም ነበር። እኔም ድምጼ ተሰለበ። በደመ ነፍስ ተከተልሁት። ሂደን ሂደን

ማርያም እያልሁ ስነበትሁ። ስውዬው በዐሥር ቀኑ ከዚች ዓለም ተለየ። አልገረመኝም። ሰይጣን በስለት ነገር ሲወጋው ዐይኔ አይቷል። ከዚያ በኋላ ያንን አካባቢ በፍጥነት ለቅቄ ሸሽሁ። ተመልሶ መጥቶ እኔንም የሚወጋኝ እየመሰለኝ ያን ሰሞን ከራሴ ጋር ተለያይቼ ሰነበትሁ። በዚያ ሰሞን በዐይነ ሕሊናዩ እየመጣ ርብሽብሽ ብዬ እንደ ነበር ትዝ ይለኛል። ውዳሴ ማርያምም አጥብቄ እጸልይ ነበር። ባላገሩ የሞተ ቀን አንድ አዝማሪ

"ጌታ ሞትሁኝ አለ፣ መነሣቱን አውቆ።

የአዳም ልጅ ቀረ እንጅ፣ ባፈር ተጨማልቆ።" እያለ ሲያለቅስ ነበር። ግጥሙን የሰማሁት በባላገሩ ልቅሶ ላይ ነው። ጌታ ሲነሣ ሰውዬው ሲሞት ሳምንቱ ተገጣጥሞ ነበር። የአዝማሪው ቅኔ ይህን ለመግለጥ የመጣ ነው።" ካለ በኋላ አከለበት።

"አሁን አሁን ሳስብ ያ መንፈስ ለባሴ ሥጋ ይመስለኛል። ጥርጣሬዬ ያ ዛር እንደሆነም መጠርጠር ጀምሬአለሁ። ነገር ግን ቁራሽ እንጀራ የማምጣት መንፈስ መሰወር ችሏል። ነገር ግን ቁራሽ እንጀራ ለመንጠቅ ይዞኝ ኃይል አልነበረውም። ቢኖረው ኑሮ መንደር ለመንደር ይዞኝ ባልተንከራተተም ነበር። ሲቀጥል ያ መንፈስ የፈለገው አብሮ መብላት ነበር። መሶቡ ሲነሣ ተቆጣ። ቁጣው የሰው ቁጣ





ዐይነት ነበር። ከዚያ በጩቤ መዘርጠጥ የሰው ጠባይ ነው። ወጣም ወረደም አሁን ላይ ሳስበው ያ መንፈስ ወይ ዕፀ መሰውር ያለው ጠንቋይ ነው ወይም ዛር የሚባለው መንፈስ ነው።" ብሎ ገጠመኙን ከሥር ጀምሮ ከተረከ በኋላ ወደስዉሩ ዓለም ታሪክ ተመለሰ።

"ብእኔ በኩል የመናው ቁራሽ ከዚህ የተለየ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ሲቀጥል በስዉሩ ዓለም ከቅዱሳንና ከጠቢባን በቀር ርኩሳን የሚኖሩ አይመስለኝም። ቅዱስ ባለበት ርኩስ እንደሚኖር ቢገመትም ርኩሱ ከጠቢባን ተሰውሮ እንደማይኖር ግልጽ ነው። እኒህ ስዉራኑ ስዉር ፍጥረታትን ስለሚያዩ ርኩስ መንፈስ ተዳብሎ የሚኖር አይመስለኝም። ጠቢባኑ ውዳሴ ማርያም ደጋሚዎች ናቸው። መናውም የተፈጥሮ መና ነው ሲሉ የኔታ በተደጋጋሚ ነግረውናል። ስለዚህ ውሳኔው መጠበቅ ነው።" ብሎ አጽናነው። ተያይዘው ስራታቸው የደቅማ ፍሬ ሲለቅሙ ወደታች ወረዱ። ከስዉሩ ዓለም የዋሸንት ድምፅ ይሰማ ነበር። ጥቂት ቆይቶ የከበሮ ድምፅ ተከተለ። ፀሐይ መጥለቅ ስለ ጀመረች ጠቢባኑ ውዳሴ እየጀመሩ ነበር። ከመኻል ሀገር ሲሄዱ በየጊዜው የሚሰማው ከበሮ እንደልማዱ ተደለቀ።

# ፳፯

ቀቢፀ ተስፋ

ሌሊቱ በጨለማ ተመርጓል:: የሰው ኮቴ በሌለበት መልክአ ምድር በጨለማ የከበደውን ዓለም ለብቻቸው ተጋፍጠውታል:: መልአከ ሞትን አምልጠው መናውን እየተመገቡ ለመኖር የጀመሩት መንገድ በጅምር ላይ ቢሆንም ተስፋቸው እንደሙጃ እየሚሸሸ ነው:: በዚህ የተነሣ አልፎ አልፎ ተስፋ መቁረጥ ቢኖርም የጸደይ ውሳኔ እየጠበቁ ቁጭ ብለዋል:: ራሳቸውን የተዋነይ ተከታይ አድርገው ጥሏቸዋል:: ተዋነያዊ መቁጠራቸው ግራ ከገባው ዓለም በር የቅኔ ቤት ታሪክ ተከትለው ይንከራተታሉ:: ስምጥ ውስጥ ይከታቸው ይሆን? ወይስ ሞት ራሱ ይሞት ይሆን? ከርታቶች ገና የተረዱት ነገር የለም:: በደፈናው ይኳትናሉ:: ቢስ ዶክተር ኄርማን መቅበራቸው ደግሞ ተስፋ አድርጓቸዋል::

"አሁንስ እየቆጨኝ መጣ::" አለ ገሞራው::

"ለምን?" አለ ታሪኩ::





"ሌሊት እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር አደረ::" አለ ገሞራው ትክዝ ብሎ ትክሻው የጎበጠ መስሏል:: ቁመቱ ኮስምኖ ያደረ ይመስል እጥፍጥፍ ብሏል::

ታሪኩም ተመሳሳይ ነው:: መስተፋቅር የመሰለ ጥርሱ ላይ የማይለየው ፍንትው ያለ ፈገግታ ብን ብሎ ጠፍቷል:: ያ በለጋ እድሜው የጎንደርን ቆነጃጅት በፈገግታው፣ ሊቃውንቱን በቅኔው ውበት ይማርክ የነበረው ፍልቅልቁ ታሪኩ አይመስልም::

ታሪኩ! "አንድ ምሥጢር ላጫውትህ?" ዐይን ዐይኑን እያዩ ጠየቀው::

"ደስ ይለኛል አጫውተኝ"

"በጸደይ ወር ፍጻሜ እሞታለሁ::" አለ ገሞራው እንባው እየተንዠቀዠቀ::

"እረ በማርያም! ሞት ሞት አሰኘህኮ! ዝም አትልም እንዴ?::" አለ ታሪኩ የራሱ የሞት ቀን መቅረቡ ትዝ ብሎት::

"አዎን እሞታለሁ:: ከመሞቴ በፊት ደግሞ ወደቅኔ ቤቴ እመለሳለሁ:: መልአከ ሞትን የመገዘቱ ምሥጢር የሚቻል



Scanned with CamScanner

አይመስለኝም፡፡" ሲለው ታሪኩንም አመመው፡፡ የማይወጡትን ዓለም ጀምረው ችግር ላይ ስለወደቁ፡፡

"እሞታለሁ ስልህ መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ ገና ልጅ ብሆንም እድሜዬን ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ቅኔ ጠላቴ ቢሆንም እንደጉድ ዘርፌዋለሁ፡፡ መወድሱን አውርጀው አውቃለሁ፡፡ ሰው ፊቱን ሲዞርብኝ በቅኔዬ እየተመሰጥሁ ክፉ ቀኔን አልፌዋለሁ፡፡ በዚያ ላይ የሞት ምሥጢር ብቻን መኖር ነው፡፡ እሱንም ለምጀዋለሁ፡፡ አብነት ትምህርት ቤት ሳለሁ ፋሲካን ለብቻዬ አክብሬዋለሁ፡፡ ለብቻዬ ቆዝሜ አውቃለሁ፡፡ ለነገሩ የትንሣኤ ቀን ብቻዬን አልነበርሁም፡፡ የሊቆች ደስ የሚል ሊቅነት በአእምሮዬ ከተፍ እያለ አብሮኝ ነበር፡፡ ለነገሩ ብቻዬን አልነበርሁም፡፡ የፋሲካ ዕለት ወፎች በፊቴ ሲዘምሩ ነበር፡፡ ለነገሩ ብቻዬን እንዳልሆንሁ እየነገሩኝ አብሬ ዘምሬአለሁ፡፡ ለነገሩ ብቻዬን አልነበርሁም፡፡ የውስጤን ደስታ የሚረዱ ውድ ውድ ምሥጢራት በአእምሮዬ እየተመላለሱ መስጠኛል፡፡ ከሽንኮር አገዳ የጣፈጡ ሐሳቦችን በአእምሮዬ ያፈለቅሁት ያን ቀን ነበር፡፡ የፋሲካ ዕለት ማለዳ፡፡ ለብቻዬ መኻል ሜዳ ቆሜ ሀገር ስታዘብ የመጡ ሐሳቦቼ ቅዠት አልነበሩም፡፡ በዚያ ላይ የሀገሬ አየር የኔ ነበር፡፡ የፋሲካ ዕለት አጥንት ሲቆረጥሙ ያየኋቸው ውሾች የእኔ ነበሩ፡፡ በሐበሻ ቀሚስ ሽር ብትን ሲሉ ያየኋቸው ውብ ውብ እናቶች የእኔ እናቶች ነበሩ፡፡ ቁራሽ





እየዘከሩ አሳድገውኛል፡፡ ይህችን ጥቂት እድሜ በፍሥሓ አሳልፌአታለሁ፡፡ ደስታ ቀመር ስለሴለው ሳልቆጥረው ቀረሁ እንጂ በዘመኔ የሥቃይ ደስታ አሳልፌአለሁ፡፡ ያለምንም ከልካይ ከጨረቃ ጋር አውግቻለሁ፡፡ የጨረቃን ምሥጢር የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ፡፡ ካሁን በኋላ ሞት ለእኔ ጌጥ ነው፡፡ ተዋነይን መሆን ካልቻልሁ የሞትን ቀን አርቆ መቅጠር ምን ዋጋ አለው? እሄዳለሁ፡፡ ቅኔ ቤት እገባለሁ፡፡ ሞት ሲመጣ እጄን ዘርግቼ እጠብቀዋለሁ፡፡" አለ ገሞራው

"ባክህ ተው! እኔ ሞት እፈራለሁ፡፡ ሞት ወደማይገባበት ሀገር ያመጣኝም ሞትን የመፍራት ጣጣ ነው፡፡" አለ ታሪኩ

"እሱማ ረጅም እድሜ መኖርን ማን ይጠላል፡፡ የድሮ ሰዎች ለፈጣሪአቸው ቅርብ ስለሆኑ ረጅም ዓመት ኑረዋል፡፡ በአዳም ዘመን በዘጠኝ መቶ ሠለሳ ዓመት መሞት በአጭር እንደመቀጨት ሆኖ ይቆጠር ነበር፡፡ በኖኅ ዘመን ደግሞ በመቶ ሃያ ዓመት መሞት በዝርዝር እንደመቀጨት ተቆጥሯል፡፡ የእድሜ ባለቤት የሆነው አምላክ ከጥፋት ውኃ በኋላ የሰው ልጆችን እድሜ መቶ ሃያ ብቻ ይሁን ሲል ሕዝብ ተንጫጭቷል፡፡ ፈጣሪ ግን የሕዝቡን ጫጫታ ሰምቶ ከተናገረ በኋላ ቃሉን አላጠፈም፡፡ ኪዳኑን ጠብቆ የሰው ልጆች እድሜ በመቶ ሃያ ዓመት ተገድበዋል፡፡ አሁን ግን



Scanned with CamScanner

መቶ ሃያ ዓመት ቀርቶ ሰማንያ ዓመት መኖር እንደብርቅ ነገር ተቆጥሯል:: ፈጣሪም ይቺን የሰው ልጅ እድሜ በሰማንያና በሰባ ዓመት ብቻ ወስኗታል:: ከሰማንያ ዓመት እድሜ በኋላ ያለው ዘመን የሞት ዋዜማ እንደሆነ መንገር ለቀባሪ ማርዳት ነው::" ብሎ ገሞራው በእንባ ተከበበ::

"ተው! ተው! የቅኔ ተማሪ ሞት ፈርቶ አልቅሶ አያውቅም:: ተዋነይ ሞትን ገዘተ እንጂ ሞት ፈርቶ አለቀሰ ሲባል አልሰማንም" ካለ በኋላ ታሪኩ ወደራሱ ሕይወት ተመለሰ::

"እኔ እድሜምኮ ረጅም እድሜ አይደለም:: መልአከ ሞትን ገዝቼ ረጅም ዓመት እኖራለሁ ብዬ ረጅም እድሜ እንደሌለኝ ከተራዳሁ ቆይቻለሁ::" ሲል ታሪኩ ተከዘ::

"እረ ባክህ ወንድሜ! ያንን ያኽልማ ልትፈላሰብኝ አይገባም:: እድሜህ አጭር መሆኑን ማን ነገርህ ባክህ?" አለ ገሞራው ታሪኩ በተናገረው እንደመደናገጥ ብሎ::

"የሞት ቀኔን በትክክል ባልረዳውም እድሜዬ አጭር መሆኑን ተረድቻዋለሁ::" አለ ታሪኩም:: ሁለቱም ተደናገጡ:: በተለይ ታሪኩ ከአቅም በላይ ተርበተበተ:: ዶክተር ኄርማን እንደ ቀበረ ገሞራውን የሚቀብር መስሎ ታዬው:: ብቻውን ሲቀር ኀዘን ሲወርሰው ሥቃይ ሲያንገላተው በፊቱ መጥቶ ድቅን





አለበት:: ገሞራው የሞተ መስሎት ብክንክን ሲል ውስጡን ተሰማው::

"እንዲህ ከሆነ ሁላችንም ፈጥነን ወደቅኔ ቤታችን እንመለስ:: ኄርማን መንገድ ላይ ቀብረናል:: እሱን የቀበርን ሰሞን የወረደብንን ሥቃይ ትረሳው አይመስለኝም:: መጽናናት የቻልነው ሁለት ስለሆን ነበር:: እኔ ሳለቅስ አንተ ባታባብለኝ ሆደ ባሻ አድርጎኝ ነበር:: አንተ ስታለቅስ መልአከ-ሞትን ገዝተን ለመኖር እንደመጣን እያነሣሁ ባላጽናናህ አሁን ለይቶልህ ታብድ ነበር:: ስለዚህ በትክክል የሞትህን ቀን ካወቅኸው ፈጥነን ወደቅኔ ቤት እንመለስ:: መኻል ሀገር ገብተን በማዕረግ መቀበር አለብን:: በዚህ ጫካ ሙተን የአውሬ ሲሳይ ከመሆን ያለፈ ነገር የለም::" ገሞራው አምርሮ ተሟገተ::

"በእርግጥ ነፍስና ሥጋዬ መቼ እንደሚለዩ ያወቅሁት ነገር የለም:: እድሜዬ ቁንጽል እድሜ መሆኑን ግን አንድ የአቡሻህር ሊቅ በግድምዳሜው ነግረውኛል:: በጊዜው በራሳቸው አስመስለው ስለተናገሩ ለእኔ የነገሩኝ አልመሰለኝም ነበር:: እየቆየሁ ግን ተረዳሁት:: በራሳቸው አስመስለው ከነገሩኝ ምልክቶች አንዱን በቀን በቀን እየተረዳሁት መጥቻለሁ::" አለ ታሪኩ::

"እረ በማርያም! ይህ ንግግር ውብ አይደለም። ሟርት መሆን አለበት። ቅዠት። ያውም የቀን ቅዠት።" አለ ገሞራው መልአከ ሞትን በንግግር ያባረረው ይመስል።

"ቅዠት ቢሆን መልካም ነበር። ነገር ግን ቅዠት አይደለም። እውን ሲሆን እያኮበኮበ ነው። ሲደርስ።." ታሪኩ ዐይኖቹን አስለመለመ።

"ብላ ንገረኝ። በትክክል ሞት የሚመጣ ከሆነ ለዐራት ዐይናው በግልጽ ነግረን ተሰናብተን ወደቅኔ ቤታችን እንመለሳለን። ሞትን ከመኻል ሀገር ሆነን እንቀበለዋለን። የሞት ሀገር ባይኖረውም የሚወዱትን ሰው ፊት እየተመለከቱ መሞት ቅንጣት ደስታ አለው።" አለ ገሞራው ከዚያ በፊት ሙቶ የተነሣ ይመስል።

"እንግዲህ በትክክል ቀኔን ማወቅ አልቻልሁም። የአቡሻህሩ ሊቅ በዋዛ በዋዛ በራሳቸው አስመስለው የነገሩኝ ምልክት ግን እየታየ ነው።" አለ ታሪኩ ዐይኖቹን እየጠረገ።

"ምንድን ነው እሱ የሞት ምልክቱ?" አለ ገሞራው ጥርሱ በለበቅ እያጸዳ።





"የሞት ምልክቱ?" ታሪኩ በምጸት መልሶ ጠየቀው። ገሞራው በድንብርብሩ ፈገግ ሲል አሻቦ የቃመ የሚመስሉ ጥርሶቹ የሞት ሳቅ ሳቁ።

"የሞቴ ምልክቱማ የዐይን ሕማም ነው። ያንተ የሞት ምልክት ጥርስ ቁርጥማት ሲሆን የእኔ የሞት ምልክት ደግሞ የዐይን ሕማም ነው።" ሲለው ገሞራው ወከክ አለ። እንደዚች ቀን ደንግጦ አያውቅም። ያስደነገጠው ደግሞ ከቅርብ ቀን ወዲህ ታሪኩ ዐይኑን እየታመመ መምጣቱ ነበር። ቅኔ ቤት ፍቅረ ቢጽ ሲመሠረቱ ሁሉም ጤነኞች ነበሩ። እየቆየ ገሞራው ጥርሴን ማለት ጀመረ። ታሪኩም ዐይኔን በላኝ እያለ ዐይኖቹን ማከክ ጀምሯል። የሁለቱም የጤና ችግር የጀመረው ከዚህ ላይ ነበር።

"በትክክል የሞት ምልክትህ የዐይን ሕማም ከሆነ እኔ በባሕላዊ መድኃኒት እፈውስኻለሁ።" አለ ገሞራው ቢጨንቀው።

"እረ ባክህ እያ! መድኃኒት ካለህ ራስህ ከቁርጥማት መዓት ተገላግለህ አላይህም? የምን በእኔ ላይ መለማመድ ነው።" አለ ታሪኩ የሞት ሳቅ እየሳቀ።

"ከሆነ መልካም ነው:: ደስታውን አልችለውም:: ዐይኔን ሊሻለኝ ይችላል:: መናው ከሌለ ግን መሞት ግድ ነው::" ብለ ታሪኩ ቀና ብሎ ድርብሩን ጨለማ እየተመለከተ:: እነሆ አሁን ጨልሟል:: ሌሊቱ እየከበደ ነው:: የስዉሩ ዓለም ከበሮም ድምፅ እየጨመረ ነበር:: የዱር አራዊቱ ሳይቀር በከበሮው ዜማ የተመሰጡ ይመስላሉ:: ካንድ ቀለብላባ ወፍ በቀር ድምፅ የለም::

ገሞራውና ታሪኩ ባንድ በኩል ዐይራት ዐይናውን በሌላ በኩል ደግሞ የመልአከ ሞትን እየጠበቁ ጋደም ጋደም አሉ:: ዛሬ ጨረቃ የለችም:: በጉም ተሸፍናለች:: በሰማይ ያሉ ከርታታ ኮከቦችም ብርሃን አልባ ናቸው:: ጥንቱንም ሰሌዳ እንጂ ብርሃን የሌላቸውም::





# ፳፱

### ከጠቢባን ውሳኔ

ዐራት ዐይናው ለመጨረሻ ጊዜ የአደጋ ጊዜ ደወል ሲመቱ ጠቢባኑ በቅጽበት ተሰበሰቡ:: ገና ቦታ ቦታቸውን ሳይዙ ዐራት ዐይናው እየቃሰቱ መናገር ጀመሩ::

"ልጆች ወደመኻል ሀገር ሂደው ሊሞቱ ነው:: ሁለቱም ብስል ስለሆነ የሚሞቱበት ቀን ጠንቅቀው ያውቁታል:: አሁን የመጣሁት የመጨረሻ ቃላችሁን ለመስማት ነው:: ይሙት ካላችሁ ይሙቱ በሉ:: ይግቡ ካላችሁ ይግቡ በሉ:: ከዚህ የተሰበሰባችሁ ሁሉ ፍረዱ:: ከዛሬ በፊት እኔ፣ ደቀኛው፣ ወይራውና ጠቢቡ ሖረ ተከራክረናል:: ዛሬ ግን አንናገረም:: ጠቢባኑ ጊዜ ወስዳችሁ ወስኑ:: የስዉሩ ዓለም ቤዛዎችም ሴቶች ተሳተፉ:: እስከዛሬ ተናግራችሁ አታውቁም::" አሉ ዐራት ዐይናው:: ጠቢባኑ ገጽ ለገጽ ተያዩ:: ወይራው ሁለቱን ተማሪዎች ወደ መኻል ሀገር ለማባረር ቆርጠው ተነሥተዋል:: ዐራት ዐይናው ግን እነሱ ከሄዱ እኔም ወደ ቡሩ ሥላሴ ተመልሼ መጽሐፍ አስተምራለሁ የሚል ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል:: አሁን የተፈጠረው ችግር ግን ድንገተኛ ነው::

"ሊሞቱ ነው ሲል ምን እያሉ ነው?" አሉ አንዱ ጠቢብ።

"እነሱ በጳደይ ወር መጨረሻ እንሞታለን። ወደመኻል ሀገር እንመለስ ሲሉ የቀልድ መስሎኝ ነበር። አምርረው ሲናገሩ ያን መጽሐፌን ገለጥሁት። ከመ ታእምርን ቀመርሁት። በትክክል ዕለተ ሞታቸውን ነገረኝ። ለእነሱ ነግሬ እንዲጨናነቁ አልፈለግሁም። ሞታቸው ግን እውነተኛ ነው። ይህንን በድግምት ሳይሆን በመጽሐፌ ቀመር መላለሼ አይቻዋለሁ።" አሉ ዐራት ዐይናው።

መጀመሪያ ጢማቸው ሐጫ በረዶ የመሰለ ታሪክ አዋቂ ጠቢብ ሲናገሩ ተነሡ። እስከ ዛሬ ተናግረው አያውቁም። ከዝምታቸው የተነሣ "አባ አርምሞ" የሚል ቅጽል ተሰጥቷቸዋል። ተነሥተው በአጭሩ ተናገሩ።

"ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነገሥታት መኳንንቱ የአብነት ተማሪዎችን በመርዳት ይታወቃሉ። ጠቢባን የሚፈልቁት ከአብነት ትምህርት ቤት እንደሆነ ጭምር ያምናሉ። ከፊል ነገሥታቱም ከአብነት ትምህርት ቤት ተነሥተው የሀገር መሪ ለመሆን የበቁ ነበሩ። ለምሳሌ በአክሱም ዘመን መንግሥት ሐናጺ ዳንኤል የሚባል ጠቢብ ነበር። የሀገራችንን ታሪክ በድንጋይ ልብ ላይ እየከተበ ድንጋይ ሲቀብር የሚኖር ጠቢብ ነበር። ለአክሱም ነገሥታት





የሥልጣኔ መምህራቸው እሱ ነው። ይህ ጠቢብ ከአብነት ቤት መገኘቱን በዐይናቸው የተመለከቱት አክሱማውያን የሀገሪቱን ሥልጣኔ የቀዱት ከአብነት ተማሪዎች ነበር። ስለዚህ ለአብነት ተማሪዎች ቀለብ በመስጠት ይታወቃሉ። እኛም ለአብነት ተማሪዎች ማዘን አለብን።

...ወደ ጎንደር ዘመነ መንግሥት ስንመጣ ደግሞ ቅድመ ፋሲልና ድኅረ ፋሲል የነበሩ ነገሥታት ለእውቀት ፍቅር ነበራቸው። ሀገር በቀል እውቀትም ያለው በአብነት ትምህርት ቤት መዳፍ እንደሆነ ተረድተው የሊቅ ፍቅር ነበራቸው። ይኸውም ሊታወቅ ትልቁ ኢያሱ ሊቃውንቱን በደብረ ሞጊና ሰብስበው እንዲፈላሰፉ ትእዛዝ ሰጥተው ነበር። ያ መንፈስ ሊየያዝ ከጃንሆይ ደረሰ። ጃንሆይም የነገሥታቱን አሰር ተከትለው የጥበብ አምላኪ ነበሩ። መኳንንቱ እንዳይከዷቸው በጋብቻ የሚያስሯቸውን ያኽል ለሊቃውንቱም ቀለብ ይሰፍሩ ነበር። ፍቅረ ሊቅነትን ከእነሱ እንማር። እኛም በአብነት ተማሪዎች ላይ ሞት መፍረድ የለብንም። ጠቢባኑን ይቀላቀሉ። ከመናው ይቅመሱ ብያለሁ።" ብለው ቁጭ ሲሉ ዐራት ዐይናው በደስታ አለቀሱ።

ቀጥሎ የደመናው ገሰሰ የቅኔ ቤት ጓደኛ ተነሡ



Scanned with CamScanner

“ባጭሩ እኔ የ "ደመናው ገሰሰ" የቅኔ ቤት ጓደኛ ነበርሁ:: እኔና ደመናው ገሰሰ ወደ ስዉሩ ዓለም የመጣው አንድ ቀን ነበር:: ደመናው ገሰሰ የጥበብ ሰው ሲሆኑ ወደ ስዉሩ ዓለም በደመና ይመጡ ነበር:: ደመናው የሚል ቅጽል የተሰጣቸውም በደመና ወደ ስዉሩ ዓለም በመመላለሳቸው ሲሆን በተጨማሪም የረጋውን ደመና በሚገጭ ጥበባቸው ከረጋው ደመና ዝናም ማዝነም ይችሉ ነበር:: ደመናውን የመዳሰስ ያኽል የደረሱ ጠቢብ ስለ ነበሩ ደመናው ገሰሰ ተባሉ:: ከዚህ ስዉሩ ዓለም መግባት ግን ተከለከሉ:: በደመናው ተመለሶ መኻል ሀገር ሲደርሱ ሞቱ:: በሰማይ ቤት እንጠየቃለን:: በምድር ደግሞ ኢትዮጵያ አንድ ጠቢብ አጥታለች:: አሁን ቢኖሩ ኑሮ አንድ ቀዳዳ ይደፍኑ ነበር:: አሁንም እኒህ ተማሪዎች ወደ መኻል ሀገር ተመለሰው ከሚሞቱ ወደ ስዉሩ ዓለም ይግቡ:: ነገ ለሀገር አንድ ውለታ ይውላሉ::” እጅ ነሥተው ተቀመጡ::

ቀጥሎ ከጠቢባኑ ሁሉ በቅኔ አንቱ የተባሉ የማዕበል ፈንቴ የቀለም ጓደኛ ብድግ አሉ:: በማዕበል ፈንቴ ሕይወት ዙሪያ መወድስ ሊዘርፉ ጥቂት ከተንጎራደዱ በኋላ መልሰው ተውት::





“ደመናው ገሰሰ ሲነሡ ማዕበል ፈንቴ ትዝ አሉኝ::” ጀምረው “ማዕበል ፈንቴ ወደዚህ ለመግባት ብዙ ጥረት አድርገዋል:: መግባት ሲከለከሉ እንደ ተራ ሰው ወድቀው ቀሩ:: ሳስበው አሁን ድረስ አንጀቴ ይላወሳል:: በእኔ በኩል እኒህ የመጡት ይቅሩና ወደ ፊት ከመኻል ሀገር ሞት ፈርቶ የሚመጣው ሕዝብ ሁሉ ስዉሩን ዓለም ቢቀላቀል ደስታውን አልችለውም:: ለጊዜው ግን ሁለቱም እኛን ይምሰሉ ባይ ነኝ::" ብለው ረስተውት እጅ ሳይነሡ ተቀመጡ::

ወደ መጨረሻ የማዕበል ፈንቴ ተማሪ የነበሩ ፊተ ቀጭን መሳይ ከርታታ ኮከብ ተነሡ:: ስለ ማዕበል ፈንቴ ጠንቅቀው ያውቃሉ::

“እኔ ከትግራይ እስከ ሸዋ፣ ከጎንደር እስከ ጎጃም፣ ከወለጋ እስከሰላሌ ከነበሩ የአብነት ተማሪዎች ጋር ቅኔ ቤት ነበርሁ:: እኒህ ሁሉ ወደዚህ መጥተው ከተመለሱ በኋላ እንደቆሉ ረግፈዋል:: ባጭሩ ከእኔ ጋር ከማዕበል ፈንቴ ቅኔ ቤት ሳለሁ በዳሞቱ ቅኔ ዘረፋ የነበሩትን ሊቆች ብቻ እንደሚከተለው ላንሣ

ነገሩ እንዲህ ነው! ጥቁሩ ፈላስፋ ጃንሆይ ባላገር ምን አለ እያሉ ያስጠይቁ ራሳቸውም ይጠይቁ ነበር:: ከሌሎች ኅቡዕ ማስረጃዎች ተነሥተው ከቅኔውም ከጥበቡም ለመቅሰም

ነበር፡፡ እናም ብዙ ተማሪ ያለው መምህር እስከ ዐሥር መስፈሪያ ስንዴ ለቀለብ ይቸረከሳል፡፡ ጥቂት ተማሪ ያለው ቀለቡም ጥቂት ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የማዕበል ፈንቴ የቅኔ ተማሪዎች ወፈ ሰማይ ነበሩ፡፡ ለማዕበል ፈንቴ ጀማሪዎቹ ሳይቆጠሩ በቅኔ ዘራፊዎች ብዛት ቀለብ ተሰፈረላቸው፡፡ የጎጃም ሊቃውንት ግን ማዕበል ፈንቴ፣ 'ማዕበል! ማዕበል!' እየተባለ በቅኔ ይሞገሳል እንጂ በጥሬ ሐቅ ሲመዘን የሚባለውን ያኽል ወፈ ሰማይ ተማሪ የለውም ሲሉ ከሰሷቸው፡፡ የዳሞቱ ዳኛ የቅኔ ተማሪዎች አስከትለው ከዋሸራ ወደ ዳሞት እንዲመጡ ሲል ማዕበል ፈንቴ ላይ ትእዛዝ ጣለባቸው፡፡ በትእዛዙ መሠረት ወደ ዳሞት መንገድ ጀመሩ፡፡ የዳሞቷ ዋና ከተማ ፈረስ ቤት ትባላለች፡፡ ስሟ አሁን ድረስ ፈረስ ቤት ነው፡፡ እንደ ሌሎች የስም ተፋልሶ አልገጠማትም፡፡ ከዋሸራ ዳሞት ለመድረስ በእግር ዐራት ሰዓት ይፈጃል፡፡ ማዕበል ፈንቴ በቅኔ ተማሪዎቹ ታጅበው ዘራፊዎች ብቻ ከዋሸራ እስከዳሞት ድረስ ቅኔ እያዘረፉ ከዋሸራ ወደዳሞት ገሰገሱ፡፡ ከከተማው ሲገቡ መወድስ ዘረፋው ከተማውን አናወጠው፡፡ ጌዴዎን እንደ አንበሳ ሲያገሳ መዘምር ሲነጥቅ ሥነ ፀሐይ መወድስ ሲደረድር ከተማዋ ድብርብሯ ወጣ፡፡ የከተማው ሰው ተነቅሎ ወጥቶ ያጨበጭብላቸው ጀመር፡፡ ዳኛውም መንፈሳዊ ዳኛ ስለ ነበሩ





አብረው እያጨበጨቡ 'አንተ ውእቱ ማዕበል! አንተ ውእቱ ነበልባል፣ አንተ ውእቱ ማዕበል' እያሉ እያጨበጨቡ አወደሷቸው፡፡ ግእዙ በአማርኛ ሲገለጽ የቅኔው ማዕበል፣ የመወድሱ ነበልባል አንተ ብቻ ነህ" ማለት ነበር፡፡ ከዚች ተአምረኛ ቀን ጀምሮ ማዕበል በሀገር በምድሩ ስመ ገናና ሆኑ፡፡ ቀለብም በእጥፍ ተሰፈረላቸው፡፡ በዳሞቱ የቅኔ ዘረፋ ከተሳተፉት የማዕበል ፈንቴ ቅኔ ዘራፊዎች መኻል

መብራቱ ዘዋድላ

ጌዴዮን ዘሸዋ

መዘምር ዘጎንደር

ተሰፋ ዘጎጃም

ሥነ ፀሐይ ዘደቅ ደሴት

ኪነ ጥበብ ዘአገው ምድር ተሳትፈዋል፡፡ እንዲያውም የጎንደሩ መዘምር እንደ ክፍለ ዮሐንስ በባዶ እግሩ እየሄደ መወድስ ሲዘርፍ ደገኞች ልብሳቸውን አንጥፈውለታል፡፡ ቅጠል ጉዝጉዘው ቅኔውን ከዚያ ላይ እንዲያፈስሰው ተማጥነውታል ይባላል፡፡ የሆነው ሆኖ እኒህ ግጨው ግጨው የቅኔ ዘራፊዎች በዳሞት የገጠር ከተማ ለያዥ ለገራዥ

አስቸግረው ነበር። ወደ ስዉሩ ዓለም መጡ። እንዳይገቡ ተከለከሉ። ሞት አጨዳቸው። መቃብር ዋጣቸው።" ብለው ታሪኩን ከሸጠሸጡት በኋላ

ወደ ኪነ ጥበብ ተመለሱ።

"ወደ አገው ምድር ሲቅ ስመለስ ዋሸራ ላይ ከማዕበል ፈንቴ ቅኔ ዘራፊዎች ስም ዝርዝር ውስጥ የመጨረሻው ዘራፊ እሱ ነበር። ልጅ እያለ የተከሰተ የጥበብ ደቀ መዝሙር ነበርም ይባላል። ከፊል ጥበቡን የቀዳው ከተስከተ ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ። ባለፈው እንዳነሣው ተከስተ ከስዉሩ ዓለም ወደመኻል ሀገር ከሄደ በኋላ በሽፍቶች ተቀጥቅጦ ሞተ። በዚያ ላይ ንጉሡ ታሪካቸውን ሲከትቡ የተከሰተን ታሪክ በምሉእ ዘለሉት። በንጉሡ ዘመን ይህ ሁሉ ታሪክ ታልፏል። ጃማይካውን በአምላክነታቸው ዝናም እንዳወረዱላቸው ያምናሉ። ኢትዮጵያውያን ተአምር ሲሉ ይጠሩታል። እኛ የስዉሩ ዓለም ጠቢባን ግን ውስጠ ወይራውን እናውቃለን። የዚህ ዝናም ምንጩ ተከስተ ነበር። ቢሆንም "ኅቡረ ናርምም" ብለን ሰምተን እንዳልሰማን ዝም ብለናል። የሀገራችን ባለ ቅኔ ጸጋየ ገብረ መድኅንም "አብረን ዝም እንበል" ያለው ይህ ምሥጢር ገብቶት ይሆን?።" ካሉ በኋላ "አሁንም እኩይ ታሪክ መድገም የለብንም። ተማሪዎች ገብተው ከመናው





ይቁረሱ። ሞት ራሱ ይሙት። ከመብራቱ ዘዋድላ እስከ ኪነ ጥበብ ዘአገው ምድር ያሉ ሊቆች ይበቃሉ። እነኚህ ብላቴዎች ወደስዉሩ ዓለም ይግቡ።" ሲሉ ጠቢባኑ "ህህህም" ብለው አጨበጨቡ።

በመጨረሻ የመልአከ ሞት መግቻው በመዳፋቸው ካለው ሴቶች መካከል አንዷት ሴት ተነሣች። ሴት ልጅ በወንድ ልጅ እንደማትጨክን ጠቢባኑ ያውቃሉ። እሷም ነገር ማስረዘም አልፈለገችም።

"ከላይ በስም የዘረዘራችኋቸው ሊቆች በሙሉ ወደ ስዉሩ ዓለም መጡ እንጂ የተዋነይን ውኃ አልቀመሱም። እነኚህ ግን የተዋነይን ውኃ ጠጥተዋል። በዚህ ደግሞ ስዉሩን ዓለም አይተዋል። ከዚህ በኋላ ቢመለሱ ምሥጢር ማውጣታቸው አይቀረም። ስለዚህ እስከ ዛሬ ሳምንት ወደ ስዉሩ ዓለም ከገቡ በሚቀጥለው ሳምንት የሞት መግቻው ከእጃቸው ይገባል። ደቀኛው ጋግረው ይሰጧቸዋል። በሚቀጥለው ሳምንት የመናው ቁራሽ ለጠቢባኑ የሚታደልበት ሳምንት ነው። እስከዛሬ ሳምንት ከእናንተ ጋር ቁጭ ብለው ይረፉ። በሚቀጥለው ቅዳሜ ላኳቸው። ያ ቀን የምሥጢር ቀን ነው።" ብላ ዝም ስትል ጠቢባኑ ዐለቱ እስኪናጋ አጨበጨቡ። በፈቃዳቸው ምላሳቸውን የቆረጡት በምልክት ቋንቋ ተናገሩ።



Scanned with CamScanner

የጦር ዕቃቸውን የሰለቡትና ሴቶች ተጨመሩት። ስልበች ቁጥራቸው ከሴት ወገን ስለሆነ በሴቶች በኩል ተሰልፈው ነበር። ደቀኛውና ወይራው በይቅርታ መንፈስ ገጻቸው ፈካ። ሖረ ተነሥተው ዘለሉ። ዐራት ዐይናው ቀለሙ ወደነገሞራው እልም አሉ። ሁለት ሊቆችን ከመልአከ ሞት መንጋጋ መንጭቀው መልአከሞትን አሳፍረዋል።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
Telegram Channel





## ፴

### ከጌርማ ጋር ቅበረኝ

ዐራት ዐይናው ክርክሩን አሸንፈዋል። ሁለቱ ተማሪዎች ወደ ውስጥ መግባት አለባቸውና የለባቸውም የሚለው ክርክር አድክሟቸው ሰነበተ። ተማሪዎችን ወግነው በመከራከራቸው ብዙ ትችት ደርሶባቸዋል። ቢሆንም ክርክሩን አጥብቀው ተከራክረው አሸንፈዋል። ወደስውሩ ዓለም ገብተው እንዲቀሳቀሱ ሲፈቀድላቸው በፍሥሓ ተጥለቅልቀው ወደ ነገሞራው ተፈተለኩ። ዐራት ዐይናው ሲሮጡ በዶቅማው በዘግባና በአጋሙ የተሰገሰጉ ወፎች ደንብረው በረሩ። "ግርርርርር" "ብርርርር" ተርርር" እያሉ ነበር። ያለ ወትሯቸው በሩጫ ብዛት በላብ ቀልጠው ሲደርሱ ገሞራውን ከየሻው አጡት። ታሪኩም የለም። በድንጋጤ እንደተዋጡ ወደ ትልቁ ዶቅማ ወረዱ። አቤት ሩጫቸው።

........

ገሞራው "ዕለቱ ሞቱ መቃረቡን አውቋል፡፡ መቃብሩን በቁመቱ ልክ ለመቆፈር ዶማውን እንደ ጨበጠ፡፡

"ቀብሬ ከዚህ መሆን የለበትም፡፡ ከታች ከዶክተር ኄርማ መቃብር አጠገብ መሆን አለበት፡፡ ሚካኤል ገዳም፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"የለም! የለም! ከዚህ ዛፍ ሥር ነው ማረፍ ያለብህ፡፡" አለ ታሪኩ፡፡

"ዶክተር ኄርማ ናፍቆኛል፡፡ ባይሆን ከአጠገቡ ማረፍ እፈልጋለሁ፡፡ በትንሣኤ ጊዜ ከዶክተር ኄርማ ጋር መነሣት እናፍቃለሁ፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"በሞት ዓለም ምን ናፍቆት አለ ብለህ ነው? አሁን ስትሞት እኔንም ሆነ ዶክተር ኄርማን እስከ መፈጠራችን ትረሳናለህ፡፡ ስለዚህ ከዚሁ ዛፍ ሥር ማረፍ አለብህ፡፡" አለ ታሪኩ

"መርሳት ልረሳችሁ እችላለሁ፡፡ ለአሁኑ ግን ዶክተር ኄርማ እየናፈቀኝ ስለሆነ ከኄርማ ጎን ማረፍ እፈልጋለሁ፡፡" አለ ገሞራው ምርር ብሎ፡፡

"የለም! የለም! መዋቲና መዋቲ ተነፋፍቀው አያውቁም፡፡ ናፍቆት የሥጋ ባሕርይ ነው፡፡ በሕይወት ላለ ሰው መዋቲው





ይናፍቀዋል፡፡ መዋቲው ግን ከሞተ ሞተ ነው፡፡ ናፍቆት የሚባል ምሥጢር የለም፡፡

ይልቁንም ናፍቆቱ የእኔ ዕዳ ነው፡፡ እንኳን አንተ ተጨምረህ ኄርማ በሕልሜ እየመጣ ናፍቆቱ ገድሎኛል፡፡ ትናፍቀኛለህ፡፡" ታሪኩ እንባውን በዐይኖቹ እየቀዳ ዝም ሲል ገሞራው የመቃብሩን አፈር በአካፋ ቦታ ቦታ እየሰጠ ከቁመቱ በላይ ረጅም መቃብር ይቆፍር ጀመር፡፡

"አልረዘመም?" አለ ታሪኩ፡፡

"ሰው ሲሞት ጋት ሙሉ ቁመት ይጨምራል፡፡ ተዘረጋግቶ ሲተኛ የሚያመጣውን ርዝመት ጨምሬበት ነው፡፡" አለ ገሞራው፡፡ በተፈጥሮ የሰው ልጅ በራሱ ክንድ ሦስት ክንድ ከስንዝር ቢሆንም ገሞራው ግን መቃብሩን ዐራት ክንድ አድርጎ ቆፈረው፡፡ ከዚያም መካነ መቃብሩ ምልክት እንዲኖረው ከትልቁ ዶቅማ ሥር አደረገው፡፡ በእርግጥ መቃብሩ ከኄርማ አጠገብ እንዲሆን ፈልጎ ነበር፡፡ ታሪኩ ተቃወመ፡፡

........

ዐራት ዐይናው ወደ ዶቅማው ሲደርሱ ገሞራው የመቃብሩን አፈር በዶማ ቦታ ቦታ ሲሰጥ አይተው ከው

አሉ፡፡ እየተርበተበቱ "በሉ! በሉ! እሱን መቃብር መልሳችሁ ድፈኑት፡፡ አፈሩን ወደ ጉድጓዱ መልሱት፡፡" ሲሉ ገሞራው ዘወር አለ፡፡ ዐራት ዐይናው ከዘግባ በኩል እየተጥመለመሉ ብቅ አሉ፡፡

"ለምን? ቀኑኮ ደረሰ፡፡ የሞት ጽዋዬን ልቀበል ምን ቀረኝ ብለው ነው?" አለ ገሞራው፡፡

"አዎን! መልአከ ሞት የሚመጣበትን ጊዜ በማወቅህ ትክክል ነህ፡፡ በዚህም ብስለትህን ተረድቻለሁ፡፡ የጥበብ ትልቁ ምሥጢር እንዲህ ዐይነቱን የረቀቀ ነገር ማወቅ ነው፡፡ ባለፈው የሞትህን ቀን ስትነግረኝ ቀልድ መስሎኝ ነበር፡፡ እየቆየ ትንሽ ትንሽ ጥርጣሬ አደረብኝ፡፡ ይህን ለማረጋገጥ መጻሕፍትን ማገለባበጥ ጀመርሁ፡፡ የደቂቀ ተዋነይን መጽሐፍ ገለጥሁት፡፡ በትክክልም የሞትህ ቀን ደርሶ ነበር፡፡ ይህንን ተከትሎ በደቂቀ ተዋነይ ዓለም ትልቅ ክርክር ተደረገ፡ ፡ በመጨረሻ ወደ ስዉሩ ዓለም እንድትገቡ ተፈቅዶላችኋል፡፡" ሲሉ ገሞራው በደስታ ወከክ አለ፡፡ ዐራት ዐይናው ቀጠሉ፡፡





እንኳን ደስ አላችሁ ልጆቼ! እንኳን ደስ አለህ ልጄ ገሞራው! ታሪኩ እንኳን ደስ አለህ!" ብለው በደስታ ከአንገታቸው ላይ ተጣመጠሙባቸው፡፡ ታሪኩ እንደ ቆመ በደስታ ፈዘዘ፡፡

እነሆ ጊዜው እየመሸ ነበር፡፡ የዛሬው ምሽት ደግሞ የተለየ ምሽት ነው፡፡ ከዚያ በፊት በነበሩ ምሽቶች ዐራት ዐይናው፣ ታሪኩ፣ ገሞራው ጉባኤ ከፍተው የልብ የልባቸውን ያወሩ ነበር፡፡ አልፎ አልፎም የእድል ፈንታ ምሥጢር ጭምር ይተነተናል፡፡ ዕድል ፈንታ ይተረጎማል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የሊቆች ጥበብ እስከ ጸባኦት ድረስ ይሰለቃል፡፡ ተያይዘው በፍሥሓ ይከንፋሉ፡፡

ሌሊቱ ኩልል ሲል ግን ዐራት ዐይናው ይሰወራ፡፡ ገሞራውና ታሪኩ ሰልቀው አድቅቀው እንደ ጨረሱ "ይህ ትውልድ ለዚህ ጥበብ የታደለ አይደለም፡፡ ኀቡረ ናርምም፡፡" ብለው ለማንም ሳይናገሩ በውሳኔ ይከረችሙታል፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተሳለፍ የፈለጉ አይመስልም፡፡ አሁን ግን ከመቃብሩ ላይ አፈር መልሰው በሞት እየዘበቱ ወደ ውስጥ ገሰገሱ፡፡



Scanned with CamScanner

# ፴፩

### የደቅ እስጢፋ ሱሪ

መቃብሩ ላይ ትኩስ አፈር ከመለሱበት በኋላ ወደጠቢባኑ መንደር እያመሩ ሳለ ዐራት ዐይናው ስለስዉሩ ዓለም ማብራራት ቀጠሉ።

"ደቅ እስጢፋ ወደ ስዉሩ ዓለም እንደመጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሱሪውን የፈታው ከዚህ ስፍራ ላይ ነበር። ሱሪውን ሲፈታ የወረደበት የድንጋይ ናዳ አስደንብሮት ከዚህ የፈረጠጠ ደቅ ማርያም ገብቷል። ቂ..ቂ..ቂ..ቂ.. በእርግጥ በደቅ እስጢፋ ዘመን የደቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገና አልተመሠረተችም ነበር።" ብለው እየሳቁ ቀና ሲሉ ጉሬዛው ከትልቁ ዛፍ ጫፍ ተንጠልጥሎ ሸንቱን ለቀቀባቸው። 'አንተ መናጢ! አንተ ምቀኛ! ወሽላህን ይቁረጠው! ወሽላ! ዕቃውን ይዘኸው ሙተህ በእኔ ላይ ትሸናለህ አይደል?' እያሉ ድቡልቡል ድንጋይ ሳጥ አድርገው ወደዛፉ ጫፍ ሲወነጭፉ ዛፉን የሙጥኝ ብለው የሚርመሰመሱ ወፎች በቅጽበት በረገጉ። ጉሬዛው ከአንዱ ዛፍ ወደሁለተኛ ዛፍ አመድረፍ ሲል አያሌ ቅጠሎች ከወፎች ላባ እኩል በነኑ። ዛፉ በአያሌው ተወዛወዘ። ወፎች "ጺው ጺው ጺው" እያሉ በሕዋው ሲበሩ መልካም ቆናተኛ ይመስሉ ነበር። ገሚሱ አራዊት እንደ አፈጣጠራቸው እየተቆጡም እየዘመሩም መንቀሳቀስ ጀመሩ። ታሪኩ ጆሮውን ለዱር አራዊቱ ዝማሬ ሰጥቶ ያደምጥ ጀመር። የዱር አራዊቱ መዝሙር የጎንደርን ወረብ ትዝ አስባለው። በጎንደር አያሌ ኀብረ ዝማሬ አሉ። በጎንደር ሊቆች የሚፈጠሩ ስርቅርቅ ወረቦች ናቸው። በጎንደር ሊቆች አገላለጽ የከንፈር ቅላጼ የመጋቤ አእላፍ ሄኖክ ወልደ ሚካኤል ሽብሻቦ እያሉ ስም ይሰጧዋቸል። ማኅሌተ ገንቦ የሚሏቸውም አሉ። እንደ ጎንደር ኀብረ ዜማ የወፎች ዝማሬም እየቅል እየቅል ነበር። ብዙ ኀብረ ዜማ ከሚፈነጥቁ አራዊቶች ቀዳሚው ያ አድባር ጠባቂ ጉሬዛ ይገኝበታል። ዐራት ዐይናውን በሽንቱ ካጠመቀ በኋላ እንደ ልቡ ይቀድስ ጀመር። ገሞራው የጉሬዛውን ቅዳሴ ሲሰማ ድሮ ጉሬዛ ቄስ ነበር የሚለው ያያቱ ተረት ተረት ትዝ ብሎት አንድ ጊዜ ዐራት ዐይናውን ሌላ ጊዜ ጉሬዛውን በአንክሮ እየተመለከተ ፈገግ አለ።

"አትቁም! ተከተለኝ። የደቅ እስጢፋን ታሪክ ልጨርስልህ። ጉሬዛውን ነገ ተነገ ወዲያ ትጠግበዋለህ።" አሉ ዐራት ዐይናው። ታሪኩ ዐይኖቹን ከጉሬዛው ሳይነቅል የአያቱን ትርክት በሕሊናው ያወጣ ያወርድ ጀመር። እንዲህ ነበር ያሉት።

“ጉራዛ በሀገራችን ክቡር ነው፡፡ አያቶቻችን የቄስ ተምሳሌት አድርገው ይገልጡታል፡፡ ስሙንም አጸድ ጠባቂ ይሉታል፡፡ በቤተ ክርስቲያን አጸድ ውስጥ አይጠፋም፡፡ ጉራዛ የቄስ ምሳሌ ሲሆን አሁን ያሉ ቀሳውስት የጉራዛው ተከታዮች ናቸው፡፡ ይኸውም ሲታወቅ ጉራዛ ጉሳን ነው፡፡ ካልነኩት አይነካም፡፡ ተንኮል ካልጀመሩት ራሱ ተንኮል አያውቅም፡፡ በቀኝና በግራ የተንዠረገገው ሐጫ በረዶ የመሰለ ጠጉሩ የቀሳውስቱ የሻሻቸው ተምሳሌት ነው፡፡ አገጩ ላይ ያረፈው ሐጫ ጢም ደግሞ የካህናቱን ነጭ ጢማና ጭራ ያመለክታል፡፡ በዚያ ላይ የጉራዛ መኖሪያው ደብር አካባቢ ነው፡፡ ከሰው ጋር መንደር መኖር አይችልም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ድረስ የቄሶችም መኖሪያ በደብር ዙሪያ ነበር፡፡ ለአገልግሎት እንዲቀርባቸው የገጠር ቀሳውስት መንደራቸውን በደብር ዙሪያ አድርገው ይኖሩ ነበር፡፡ የዲማ ካህናት በደብሩ ዙሪያ ተረግርገው የልዳውን ሰማዕት ሲያገለግሉ እድሜ ልካቸውን እንደኖሩ አውቃለሁ፡፡ የጎንደር ካህናት በደብረ ብርሃን ጥግ ሰፍረው ይኖሩ ነበር፡፡ ደብረ ብርሃንን እንደዐይን ብሌናቸው ለመጠበቅና ከክፍለ ዮሐንስ ቅኔ ለመቀጸል እንዲሰልጣቸው ነው፡፡” እያሉ አያቱ ያወጉትን ለማስታወስ ከእርምጃው ጥቂት ገታ ሲያደርግ ዐራት ዐይናው የደቅ እስጢፋን ታሪክ መተረክ ቀጠሉ፡፡ ገሞራውም ከሐሳቡ ተናጠበ፡፡





“ደቅ እስጢፋ ሲመጣ መጀመሪያ ያረፈው ከዚህ ስፍራ ላይ ነበር፡፡ አበው እንደሚተርኩት ኩሻውያን ጠቢባን በዚህ መኖራቸውን ሰምቶ ወደ ደቅ መጣ፡፡ ደቅ ገብቶ ሰዉራንን እየፈለገ ሳለ ከዚች ስፍራ ደረሰ፡፡ ከዚች አፈር ላይ ቁጭ ብሎ ወገቡን ሲፈትሽ ሱሪውን ፈታ፡፡ በዚህ ጊዜ ይህ ጉራዛ ሽንቱን ለቀቀበት፡፡ ጉራዛውን ለመግመስ ድንጋይ ሲያነሣ የድንጋይ ናዳ ወረደበት፡፡ ድንጋዩ ሲወረወር እንጂ ወዴት እንደሚመጣ አላወቀውም ነበር፡፡ ጠቢባኑ ድንጋጤውን ሲተርኩ ጥርስ አያስገጥሙም፡፡” አሉ ዐራት ዐይናው፡፡

“ማን ነው የድንጋይ ናዳ ያወረደበት?” አለ ታሪኩ፡፡

“ከሰዉራኑ አንዱ ይሆናል እንጂ፡፡ ማንም ሰው ከዚች ላይ ወገቡን መፈተሽ ይቅርና ምራቁን መትፋት አይችልም፡፡ ደቅ እስጢፋ ግን ያን ባለማወቅ ሲጸዳዳ ሱሪውን ፈታ፡፡ ጉራዛው ሽንቱን ለቀቀበት፡፡ ከጠቢባን አንዱ የድንጋይ ናዳ አወረደበት፡፡ ሱሪውን እንደ ጨበጠ በድንጋጤ ክው አለ፡፡ አሁንም ድጋሜ የድንጋይ ናዳ አወረደበት፡፡ ደንግጦ ከዚህ የሮጠ ደቅ ማርያም አረፈ ይባላል፡፡ አሁንም ይህ ጉራዛ ሽንቱን የለቀቀው ሥራው ስለሆነ ነው፡፡ እንግዳ ሰው ወደዚህ ስፍራ ሲመጣ በወዙ ያውቀዋል፡፡ አስቀድሞ ሽንቱን ይለቅበታል፡፡ ከዚያ በኋላ

እንግዳው ከዚህ ስፍራ ቁጭ ብሎ ሱሪውን ፈትቶ ወገቡን መፈተሽ አይችልም።

ደቅ እስጢፋም የገጠመው ያ ታሪክ ነበር። ከዚህ በር ጀምሮው ወደውስጥ ወገብን መፍተሽ የተከለከለ ነው።" ቀና ብለው ጉሬዛውን ተመልክተው "ይህ ጉሬዛ የዋዛ ጉሬዛ አይደለም። ምንም በራሴ ላይ ቢሸናብኝም ልቀየመው አልችልም። እሱ ሥራውን እየሠራ ነው።" ካሉ በኋላ ጥቂት አለፍ ብለው ቁጭ አሉ። ድካም ቢጤ ስለተሰማቸው አርፈው ለመነሣት ነበር።

ጥቂት ዕረፍት አድርገው መዞር እንደጀመሩ "ቡልቅ ቡልቅ" ከምትል አዲስ ምንጭ ጥግ ደረሱ።

"ይቺ ውኃ ከመነሻዋ ጠበል ናት። ዝቅ ስትል በተራ ውኃነት ማንም ይጠቀማታል። ከዚህ ስፍራ ላይ የመሰወር ምሥጢር ጭምር አላት። እንደ ተዋነይ ውኃ የመሰወርም የመከሰትም ጥበብ አላት። የመኻል ሀገር ሰዎች የውኃዋን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቁታል። ድሮ ከወሎ ከሸዋ ከትግራይ ከጎንደር ከጎጃም ቅኔ ቤቶች ይችን ውኃ ለመፈለግ ያልመጣ የቅኔ ተማሪ የለም። ውስጥ አዋቂዎችን ጨምሮ ወደዚህ ጫካ ውስጥ በየጊዜው ብቅ ያሉ ሰዎች በዚች ውኃ ግርምት እንዳደረባቸው ይናገራሉ። ይቺን ውኃ አሁን ስትንፎለፎል





አገኘናት። ስንመለስ ግን በቦታዋ ላትኖር ትችላለች። ለማንኛውም አንድ የሆነ መለያ ምልክት ማስቀመጥ አለባችሁ። ምልክት አስቀምጡና ወደፊት እንቀጥል።" አሉ ዐራት ዐይናው።

ታሪኩ ደበሎውን አውልቆ ከምንጯ አጠገብ ካለው ረጅም ዛፍ ካንጠለጠለው በኋላ ተከተላቸው። ከፊል ጉራንጉሩን አንድ ባንድ ዞረው አስጎብኝተው ከፈጸሙ በኋላ ወደማታ ወደምንጯ ተመለሱ። ከደበሎው በቀር ምንጯ የለችም። ውኃዋ ቀርቶ መውረጃዋ እንኳን አልተገኘም። ታሪኩ እየተደነቀ ደበሎውን ከዛፉ አንሥቶ ተከተላቸው። ወደ ዘግባው ዘለቁ። ወደ ጠቢባኑ ሊደርሱ እየተቃረቡ ነበር።

# ፴፪

## ከዝግባው ሥር

ከጠቢባኑ በር ከትልቁ ዘግባ ሥር ሲደርሱ ገሞራውና ታሪኩ ሕልም ሕልም መሰላቸው። በፍሥሓና በፍርሐት የልብ ምታቸው ሲጨምር እየተሰማቸው ነበር። ግራ ቢገባቸው ጠቢባኑ ጉባኤ አድርገው እስኪቀበሏቸው ድረስ ከዘግባው ሥር ቆመው የደቅን ታሪክ አነሡ።

"ደቅ እስጢፋ ለምን ተባለ? በዚያውስ ላይ ደቅ እስጢፋ ማን ነው?" አለ ገሞራው። ዐራት ዐይናው ቀና ብለው በአግራሞት ከተመለከቱት በኋላ

"ውስብስቡ ታሪክ የሚጀምረው ከዚህ ላይ ነው።"

"እንዴት?"

"ስለ ደቅ እስጢፋ ሦስት መሠራታዊ የታሪክ እሳቤዎች አሉ። የመጀመሪያው እሳቤ ደቅ እስጢፋ የተዋነይ የቅኔ ቤት ስሙ ሲሆን ተዋነይ ደግሞ የጥበብ ስሙ ነው ብለው የጻፉ አሉ። በሁለተኛው እሳቤ ውስጥ ያሉ ሊቆች ደግሞ ዐጤ እስክንድርን ቅኔ ያስተማረው ሌላ ደቅ እስጢፋ ነው ይላሉ።





ይኸውም በዐሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ባለቅኔ ነው ሲሉ ይከራከራሉ። የመጨረሻው ታሪክ ግን ጆሮ ይሰባል። እኔንም ሊያሳምነኝ የቻለ ግዙፍ ታሪክ ነው። እነሆ ተቀበሉ።" ብለው በማጋነን ቀጠሉ።

"እሱ ምን መሰላችሁ? ለዐጤ ካሌብ ሁለት ልጆች እንደ ነበሯቸው ግልጥ ነው። እኒህም ገብረ መስቀልና ዘእስራኤል ናቸው። ሁለቱም በነገሥታት ታሪክ ስማቸው ተጠቅሷል። ዐጤ ገብረ-መስቀል መንግሥታቸውን ሲወርስ ዘእስራኤል ግን የደረሰበት አልታወቀም። ስለአክሱም ዘመኑ መንግሥት የሚተርከው ክብረ ነገሥትም ወዴት እንደደረሰ ማብራሪያ አይሰጥም።" ካሉ በኋላ

"አንዳንድ የታሪክ ሊቆች ይቺን ጫፍ ይዘው ዘእስራኤል ተሰውሯል። በስዋሬ እያለ ደግሞ ደቅ እስጢፋን ወልዷል። የተሰወረበት ስፍራ ደግሞ ደቅ ነው ይላሉ። ስዋሬውም የአስማት ሳይሆን የተፈጥሮ ስዋሬ ነው ሲሉ መኻል ሀገር አለማ ነበር። ገሚሶች ደግሞ ዐጤ ካሌብ ሁለት ልጆቻቸውን በገሀዱና በስዉሩ ዓለም አንግሠቸዋል። በገሀዱ ዓለም ዐጤ ገብረ መስቀል ሲነግሥ በስዉራኑ ዓለም ደግሞ ዘእስራኤል ነገሠ። ዘእስራኤል ደቅ እስጢፋን ወለደ። የደቅ እስጢፋ ልጆች በዚህ መኖር ቻሉ። ስማቸውም ደቅ እስጢፋ ተባለ።



Scanned with CamScanner

ደቅ ማለት በግእዝ ቋንቋ ልጆች ማለት ነው። የትግራይ ልጆች "ደቂ አሉላ፣ ደቂ ተንቤን" ይላሉ። የአሉላና የተንቤን ልጆች ማለታቸው ነው። በከፊል እኔ የማውቀው የደቅ እስጢፋ ታሪክ በወፍ በረር ይህንን ይመስላል።" ጥቂት ፋታ ወስደው አከሉበት።

"የታሪኩን ተአማኒነት አሜን ብለው የተቀበሉ ከፊል የትግራይ ልጆች ጥበብ ለመፈለግ ወደስፍራው በብዛት ይመጣሉ፤ ይሄዳሉ። ይህን እናንተም ታውቁታላችሁ። ቅኔ ቤቷን ለረገጠ አዲስ ነገር አይደለም። እያሌ የቅኔ ተማሪዎች የሚጎርፉበት ስፍራ ነው ደቅ እስጢፋ። ሌላው ቀርቶ ሀገሪቱን ባንድ ወቅት የመሯት የትግራይ ልጆች ሳይቀር ይህ አፈ-ታሪክ እንዲመረመር ፍላጎት ነበራቸው። ለዚህ ደግሞ የምርጫ ምልክታቸው ያስረዳል።" አሉ ዐራት ዐይናው የምርጫ ምልክታቸው ንብ በመኻል ሀገር ዘወር ዘወር ሲሉ የምርጫ ምልክታቸው ንብ መሆኗ እርሳቸው ከሚያውቁት ምሥጢር ጋር ተገጣጥሞላቸው።

"እንዴት? እንዴት?" አለ ታሪኩ ትንቢት ከሆነ ብሎ። ዐራት ዐይናው ግን ታሪክ እንጂ ትንቢት እያወሩ አልነበረም።





"ሀገር እንደሚያውቀው የምርጫ ምልክታቸው ንብ ነበረች። ይቺን ንብ በዘፈቀደ የመረጧት ተራ ንብ አይደለችም። ታሪኳ ከደቅ ታሪክ ጋር ይያዛል።"

"ማለት?" አለ ገሞራው

"እንደምትመለከቱት ሀገሩ የንብ ጉራንጉሬ ነው። ከዶቅማው እስከ እሼው ደረስ ረጃጅም አርዘ ሊባኖሶች የንብ ጉራንጉሬ ናቸው። ንቦች በየጉራንጉሬው ማር ይሠሩባቸዋል። በስዋሬ ያሉ እየመነተፉ ይጠቀሙበታል። የትግራይ ልጆች ንብን ለምርጫ ምልክት ማቅረባቸው ከላይ ከላይ ትጉሕ ነን እንደንብ ተግተን እንሠራለን ለማለት ቢመስልም ውስጡ ግን ወደፊት ተሰውረን ነጻነታችንን ጭምር እናስከብራለን። የእስጢፋ ልጆች ነን ማለታቸው እንደሆነ ይወራል። ይኸውም ሲታወቅ ያለፈው መሪ ከዚህ ስፍራ ድረስ በሄሊኮፍተር መጥተው ነበር። ባለቤታቸውም በሁለት ሺህ ዐራት ግድም ከአዲሳባ ሱዳን ድረስ የሚዘልቀውን ሀገር አቋራጭ መንገድ የሚጎበኙ መስለው በቋራ በኩል ወደዚህ ለመግባት ሞክረው ነበር። በወቅቱ ቋራ በወታደር ተከቦ ከሰነበተ በኋላ ወደዚህ ስፍራ ብቅ ሳይሉ እንደተመለሱ አውቃለሁ። እኔም ያን ቀን ወደ ቋራ ብቅ ብዬ ነበር። የሄድሁት ሰባኬ ወንጌል መስዩ ነው። ከቋራ ከተማ ወጣ ብዬ

ካንዲት ዛፍ ሥር ቁጭ ብዬ ሁኔታውን መከታተል ጀመርሁ፡ ፡ በትክክልም የወንጌል መምህር ለመመሰል ሞክሬአለሁ፡፡ ቀን ቀን ከዛፍ ሥር ተሸብልዬ ተኝቼ ሁኔታውን ሳዳምጥ እየዋልሁ ወደምሽት ከዛፍ ሥር ጥቂት ምእመናን እየሰበሰብሁ መስበክ ጀምሬ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ታሪኬ ነው፡፡ በኋላ ቀዳማዊቷ ወደአዲሳባ ሲመለሱ እኔም ወደቤቴ ተመለስሁ፡፡ ወደዚህ ስዉሩ ዓለም ለምን እንዳልመጡ ግን ላውቅ አልቻልሁም፡፡" አሉ ቀለሙ

"እረ በማርያም!" አለ ገሞራው በአንክሮ፡፡

"እውነቴን ነው! አሁንም ላይ የጉምዝ ምድር የጦር ቀጠና የሆነበት ምሥጢር ይኸው ይመስለኛል፡፡ ምሥጢሩን ግን አሁን ላይ በዙፋን ያሉት መሪም የሚያውቁት አይመስለኝም፡ ፡ ከእግዜር በቀር ይህን የሚያውቅ የቤተ መንግሥት ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡" ካሉ በኋላ ድሮ ወደሚያውቁት ወደቅኔ ቤቱ ታሪክ ተመለሱ፡፡

"ድሮ ቅኔ ቤት ሳለን ሁላችንም ይህን ስፍራ በጥብቅ ፈልገነዋል፡፡ ከተነዋይ ታሪክ ተነሥተን የመሰወር ጉጉት ነበረን፡፡ በተለይ የትግራይ ሊቆች የቀለም ጓደኞቼ ጎንጅ ደብረ ጥበብ ቅኔ ተምረው ሲፈጽሙ ደቅን ሳይሳለሙ ወደ ትግራይ አይመለሱም ነበር፡፡ ጎንጅ መወድስ ዘርፈው በቅኔ





መምህርነት ከተመረቁ በኋላ በሣኒታው ወደደቅ እስጢፋ የሚመጡ የትግራይ ልጆች እልፍ አእላፍ ነበሩ፡፡ ከቅርብ ቀን ወዲህ ግን መምጣት አቁመዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ የስዋሬው ወሬም እየደበዘዘ የመጣ ይመስለኛል፡፡ እናንተ ግን መልካም መርጣችኋል፡፡ ምርጫችሁን አከብራለሁ፡፡ እኔም ለተዋነይ ጥበብ መርጫችኋለሁ፡፡" ሲሉ ገሞራው በፍሥሓ ተዋጠ፡፡ ታሪኩ የወፎችን ጣዕመ ዜማ እየሰማ ያዳምጣል፡፡ ዐራት ዐይናው ከአንዱ ታሪክ ወደሌላው ታሪክ ዘለሉ፡፡ ወደስዉሩ ዓለም ሴቶች ጥቂት ማለት ፈልገው፡፡

"በደቅ እስጢፋ ውስጥ ሁለት ምሥጢራት አሉ፡፡ ቀዳሚው በሴቶች መዳፍ የሚገኘው የሞት መግቻው ነው፡፡ የመልአከ ሞትን መግቻ በቀላሉ ማብራራት አልችልም፡፡ በደቅ ውስጥ ባሉ ሴቶች መዳፍ ያለ ሲሆን በመኻል ሀገር ከነበሩ ሊቆች ተዋነይ ብቻ እንደተጠቀመበት ይነገራል፡፡ ከምን እንደሚሠራ ከጥበብ ሴቶች ትረዳላችሁ፡፡ የሞት መግቻው ያ ነው፡፡ "ጎብስተ መና ይባላል"፡፡ የሚገኘው ደግሞ በስዉሩ ዓለም ባሉ በሴቶች እጅ ብቻ ነው፡፡ እሱን ከሴቶች ዓለም ስንደርስ ከሴቶች እጅ ታገኙታላችሁ፡፡ ተከተሉኝ!" ብለው ስዉሩን ዓለም በጥበብ ዐይን እያስጎበኙ ታሪኩን ቀጠሉ፡፡



Scanned with CamScanner

"የድሮ የቀመር ሊቆች ወደፊት ኑሮ እሳት ይሆናል፡፡ በዚያ ዘመን ለኢትዮጵያ ሰዎች የመናው ቁራሽ ይገለጣል እያሉ ያወሩ ነበር፡፡ ጊዜው የደረሰ ይመስለኛል፡፡ ወንድሜ ፋሪስ ከጻፈው ደብዳቤው ውስጥ "ቀመሩም እየደረሰ ነው" የሚለውን ቃል ሳነብ ምን ያኽል እንደ ደነገጥሁ የማውቀው እኔ ነኝ፡፡" ብለው "ቀጥሎ የምንሄደው ወደ መና መጋገሪያው ነው፡፡ መና ጋጋሪው ደቀኛው ይባላሉ፡፡ በስዉሩ ዓለም ደቀኛው መልአክ የሚል ቅጽል ጭምር አላቸው፡፡ በደመና እየተጫኑ ወደመኻል ሀገር ብቅ ጥልቅ ማለት ያበዛሉ፡፡ ከዓመታት በፊት ጎንደርን ሊገበኙ ሄደው ነበር፡፡ ያን ቀን ደግሞ በጠራራው ቀን ፀሐይ የጨለመችበት ዓመት ነበር፡፡ ከጎንደር መልስ ለምን ፀሐይ በጠራራው ቀን እንደ ጨለመች ከአቡሻህር ቀለም ያስረዱኝ እያሉ ሲዘበዝቡኝ ከረሙ፡፡ ዱሩ ብነግራቸው ባስረዳቸው ሳይገባቸው ቀረ፡፡ የአቡሻህር ቀለም ክፍላቸው አይደለም፡፡ በልደት ቀናቸው ተረድቸዋለሁ፡፡" ብለው ስለደቀኛው ከተረኩላቸው በኋላ

"አሁን ወደ እሳቸው እሄንዳለን፡፡ መናውን እንዴት እንደሚጋግሩት ከደቀኛው ትረዳላችሁ፡፡" ተርከው እንዳበቁ ወደ ደቀኛው ገሰገሱ፡፡





## ፴፫

### ደቀኛው

ገሞራውና ታሪኩ ወደጎበኙት መናው መጋገሪያ እንደ ደረሱ ደቀኛው በስርቅታ ተመለከቷቸው፡፡ እድሜአቸውና ብስለታቸው እየቅል ኾነባቸው፡፡ ከእሳቸው እድሜ ጋር ሲነጻጸሩ የአምስት ዓመት ኩታራ መሰሏቸው፡፡ በተለይ የገሞራው ፊት የሐምሌ ሰማይ ፊት ቢጤ ነው፡፡ ጨፍግጓል፡ ፡ "ይህ ቀንጃ ፊት ብቻ!" አሉ ደቀኛው በውስጣቸው፡፡

ከዚያም

"ክርታታ ኮከቦች ሆይ! እንኳን ደስ አላችሁ! ወደስዉሩ ዓለም እንዳትገቡ አጥብቄ የተከላከልሁት ሰውዬ እኔ ነበርሁ፡፡ አሁን ግን ከልቤ ተቀብያችኋለሁ፡፡ እኔ ሐሽማል ነኝ፡፡ ሐሽማሎች ሽንገላ አናውቅም፡፡ ይቅር በሉኝ! ክርታቶች ሆይ! ይቅር በሉኝ! ኮከቦች ሆይ ይቅር በሉኝ" ብለው ከገሞራው እግር ሥር ሊወድቁ ወደመሬት ሽብረክ ሲሉ ገሞራው ተፈናጥሮ ወዲያ ደረሰ፡፡ ታሪኩ በድንጋጤ ደነዘዘ፡፡ ዐራት ዐይናው ከመሬት ላፍ አድርገው አንሥተው

"ይቅር በሏቸው" አሉ። "ይቅር ብለናል። ይቅር ብለናል። ድሮም ቂም አልያዝነም! ይቅር ብለናል።" ሲሉ

"ይበሉ ይነሡና የመናውን ምሥጢር በከፊል ይንገሯቸው" አሉ ዐራት ዐይናው ደቀኛው የኀብስተ መናውን ምሥጢር በከፊል ማብራራት ጀመሩ። በግእዝ ቋንቋ።

"በዚህ ውስጥ ያለው መና ከሰማይ የወረደ መና አይደለም። ምድራዊ ሲሳይ ነው። የኢትዮጵያ አፈር ያፈራው መና ነው። እኛ ጠቢባን ደቂቀ ተዋነይም ከሰማይ የወረደ መና ተመግበን አናወቅም። እኛም በጠቢብነት እንጂ በመንፈሳዊ ብቃት ከአበው አንደርስም። በቅድስና ከእኛ በላይ ያሉ ሰብእናቸው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተሞላ አበው መና ከደመና እንደሚወርድላቸው ገድላቸውና ድርሳናቸው ይናገራል። ያንን እየተመገቡ ፈጣሪያቸውን ሲያወድሱ ይኖራሉ። እኛ ግን በመዓርግም ሆነ በክብር ከእኒህ በታች ነን። ምግባችንም ምድራዊ ነው። ከኢትዮጵያ ቅዱስ አፈር የተገኘ ዐፈር ነው። ምሉዕ ታሪኩን ከሴቶች ጋር በሚኖራችሁ ቆይታ ትረዱታላችሁ። የሴቶች ድርሻ ነው። የሞት መግቻው እኛ ወንዶች ሳንሆን ሴቶች ተመራምረው ያገኙት መና ነው።" ብለው ወደ ገሞራው ቀና አሉ። ዐይኖቹን ገርበብ አድርጎ ተመስጦ ላይ ነበር። ልማዱ ነው። ይህንን ያኽል ምሥጢር





ሰምቶ ይቅርና ተራ ነገሮችን ጭምር ወደ ውስጡ ሲመዘግብ ዐይኖቹን ገርበብ ማድረግ ይቀናዋል። በዚህም ከአቡነ ጳውሎስ ጋር ተመሳሳይ ነው። አቡኑም ከልባቸው ሲያዳምጡ ዐይናቸውን ገርበብ አድርገው ነበር። ታሪኩ ግን መስተፋቅር የተኳሉ የሚመስሉ ዐይኖቹን ይበልጥ አፍጥጦ ይመለከታቸው ነበር። የጎንደርን አብያተ መንግሥት ሲጎበኙ በመጡ ጊዜም ይኸው ነበሩ። ለውጥ የለም።

ደቀኛው ቀጠሉ። "በእርግጥ መኻል ሀገር መና ያወርዳሉ እየተባልን እንደምንታማ አውቃለሁ።" አሉ ደቀኛው።

"የሐበሻ ሐሜት መቼም በሁሉም አለ። እኛም መና ከደመና ያወርዳሉ እየተባልን እንደምንታማ አውቃለሁ። ይህ ግን አጓጉል ቅጥፈት ነው። መና ከደመና አናወርድም። በእርግጥ ይህ መና ስሙን ከሰማይ ከሚወርደው መና ወርሷል። በግእዝ "ኀብስተ-መና" ይባላል። በአማርኛ "የመና ቁራሽ" ማለት ነው። በሴቶች መዳፍ እንደ ልብ ይገኛል።" ምጣድ ሲጥዱ እየተጣደፉ ንግግራቸውን ገታ ሲያደርጉ

"ተመሳሳዩ መኻል ሀገርስ የለም?" አለ ታሪኩ



Scanned with CamScanner

"በየሀገሩ ሊኖር ይችላል። ሰው ግን የለም። ማለቴ ሰው ብቻውን ሰው አይደለም። ጥበብና ጠቢብ የለም ማለቴ ነው።" አሉ ደቀኛው።

"እረ ጠቢባንም አሉ። ሀገር ምድሩን የሚያውኩ ጠቢባን ተርፈዋል።" አለ ገሞራው

"የሉም! አዛኚቷን! የሉም!" አሉ ደቀኛው።

"በድሮ ዘመን መና ከደመና በተአምራት ይዘንብ ነበር። ያ መና ግን መምጫው አይታወቅም። ለሙሴ በሃይማኖቱ ጽናት ተሰጥቶታል። ይህንንም ተአምራት ሲል ጽፎታል። ተአምራት የሆነው ደግሞ መምጫው ስላልታወቀ ነው። በአምላካዊ ትእዛዝ የመጣ በመሆኑ የአይሁድ ሊቆች "ተአምራት" ሲሉ ጠርተውታል። መናው በቤተ መቅደስ ይኖር እንደ ነበር ቶራ ይተርካል። የእኛ ሊቆችም ይህን መና ጌታ እስኪመጣ ቤተ መቅደስ በመሶበ ወርቅ ይኖር ነበር። አማናዊው መና ክርስቶስ በአምሳለ-ኅብስት ሲሰጥ ግን መናው የደረሰበት አልታወቀም ሲሉ ተርከዋል። ያ መና ይሆን የዚህ ስዉር ዓለም ኅብስተ መና?" አለ ገሞራው።

"የለም! የለም! እኔ በቀለሙ ትምህርት በኩል ውሽልክ ቢጤ ነኝ። እንደቀለሙ ጠልቄ አልተማርሁም። ይህን





ጥያቄ ከዐራት ዐይናው ጠይቁ።" ብለው ምጣድ ለመጣድ ይጣደፉ ጀመር።

የመናው መጋገሪያ ምጣድ የድኃ አውድማ ያክላል-ስፋቱ። እሳቱ ሲንቀለቀል ጢሱ ከደቅ ጉም ጋር ጣራ ሠራ። ምጣዱን አስተካክለው ጉልቻውን እንደጉለቱ

"እንግዲህ ይህ ከላይ ያነሣኸው ምሥጢር ሃይማኖታዊ ምሥጢር ነው። ወደ እኛ ወደጠቢባኑ ስንመጣ ግን የደቅን ምሥጢር ብቻ እናነሣለን። የመናውን ቁራሽ እናምጣው።" ብለው ምጣዱ ፍም እስኪመስል ያሞቁ ጀመር። ፍም ሊመስል ድቡልቡል ድንጋይ የመሰለ ነገር ከአንድ ድንጋይ ሥር አነሡ። በመኻል ዐራት ዐይናው ጣልቃ ገብተው

"ይቺን ድንጋይ ተመልከቱ።

"ዶንሳ ተረጅልኝ እመኒ ይልማና።

"ድቡልቡሉ ድንጋይ መና ሁኗልና።" የሚለውን ምሥጢር ታስረዳለች።" አሉ። ገሞራውና ታሪኩ ምን እንዳሉ አልሰሟቸውም።

"እረ የኔታ! እኔ እምፈልገውኮ ድንጋይ አይደለም። ድንጋይ ምን ይሠራልኛል? እኔ እምፈልገው ድንጋዩን መና አድርገው



Scanned with CamScanner

ሲጋግሩ መመልከት ብቻ ነው። መኻል ሀገር ሳለሁ ድንጋዩ መና ይሆናል እያሉ ሲያጓጉኝ ኑረዋል። ጥበቡን ንገሩኝ ስላቸው ክርታታ ኮከብ ካልሆንህ አይቻልም እያሉ ለዓመታት አድክመውኛል። ወደዚህ የመጣሁት ያንን ለመፍታት ብቻ ነው። ድንጋዩን መና አድርገው የሚመግቡኝ ከሆነ በጥበብ አምናለሁ። በቀር ተዋንያችሁን ይዛችሁ ኑሩ። እኔም አለማወቄን ይዤ እኖራለሁ።" አለ ገሞራው ከልብ እንዲነግሩት ፈልጎ። ዐራት ዐይናው ዝም ሲሉ ደቀኛው ፈገግ ብለው ቀጠሉ።

"አለማወቅህን የሚነካብህ የለም። ለዘለዓለም ተሸክመኸው ትኖራለህ። ብዙኃኑ ያለማወቃቸው እንዳይገለጥባቸው ሊቅ መስለው በሚኖሩባት ሀገር ልሙጥ ሊቅ መምሰል ጌጥ ሆኖ ቀጥሏል። መምሰል እንጂ ሊቅ መሆንን ግን ውኃ በልቶታል። እኔም ኢማእምርነትህን አከብራለሁ። አልነካብህም።" ካሉ በኋላ ፈገግ እያሉ

"ለማንኛውም ይህን ድንጋይ መሰል ነገር፣ በሀገር ያለው ልሙጥ ድንጋይ አይደለም። የማር ሰፈፍ የሚመስለው ከማር ስለተሠራ አይደለም። የመናው ቁራሽ ነው። በመኻል ሀገር ድንጋዩ በጥበብ ዳቦ ይሆናል የሚለው ነገር ሊያስስታችሁ አይገባም። የሀገራችን ድንጋይ፣ ድንጋይ እንጂ





ዳቦ ቆሎ አይደለም። ደረቅ ድንጋይ ነው። ይህ ግን ድንጋይ አይደለም። መናው ነው። የመናው ቁራሽ ማለት ይኸው ነው። ምጣዱ በደንብ እስኪግም ጠብቅ። ይህንን ድንጋይ መና አድርጌ..." ወደምጣዱ ሥር እንገታቸውን ዘንበል አድርገው እሳቱን ቡፍ ቡፍ ቡፍ ሲሉ እሳቱ እንደደመራ እሳት ተንገረገረ።

ድንጋይ መሳይ መናውን ከመኻል እጃቸው ላይ እያንከባለሉ ማብራራት ቀጠሉ።

"ይህን ድንጋይ ከዚያ ማዶ ዐለት የተፈለጠ ድንጋይ አይደለም። እሺ!"

"እሺ አባቱ!" አሉ ሁለቱም ዐይናቸውን ከምጣዱ ላይ እንደጣሉ።

"መድኃኔ ዓለም እሺ ይበላችሁ! እንግዲህ ተመልከቱ! ይች ጠጠር ድንጋይ ከምጣዱ ልብ ላይ ስታርፍ መቅለጥ ትጀምራለች። መቅለጥ ስትጀምር እንደሊጥ በምጣዱ ልክ ማዞር ብቻ ነው።" ብድግ አድርገው ከምጣዱ መኻል ልብ ላይ ቁጭ ሲያደርጓት በቅጽበት ምጣዱ ድምፅ አወጣ። "ተሸሸሸሸሸሸሸ" ሲል ድንጋይቱ መፍለስ ጀመረች። ኀብስተ መና ማለት ይህ ነው። እሺ!"



Scanned with CamScanner

ደቀኛው እጆጌአቸውን ወደትከሻቸው ሸብሸብ አድርገው በምጣዱ ልክ አዙረው ከጋገሩት በኋላ ምጣዱን ገጠሙት። ለአፍታ ቆይተው ምጣዱን ሲከፍቱት ትኩስ እንጀራ በግ አሰ፡ ፡ መናው ነው። የዐይኑ ስፋት የእንጀራው ጥራት በትክክል ከሰማይ የወረደ ይመስላል። ታሪኩ ራሱን ስቶ ወደቀ። ገሞራው መብራት እንደያዘው ሰውነቱን ነዘረው። ሊወድቅ ተንገዳገደ ቀረ።

ዐራት ዐይናው ታሪኩን አፈፍ አድርገው አነሡት። ደቀኛው ግን ሥራ አልፈቱም። ደግመው ደጋግመው ትኩስ ትኩሱን እንጀራ ከምጣዱ እያወጡ ደረደሩት። ቤቱ የሠርግ ቤት መሰለ። የመናው መዓዛ ሰዉሩን ዓለም አወደው።

"ይበሉ ዐራት ዐይናው! የከርታታ ኮከቦችን ታሪክ ያስተምሯቸው። የከርታታ ኮከቦችን ታሪክ ሲረዱ የመናው ምሥጢር ይገባቸዋል። ከዚያም ከሴቶች የጥበብ ዓለም እንወስዳቸዋለን። ከሴቶች እጅ መናውን ከተቀበሉ በኋላ እኔ በዚህ ምጣድ እጋግርላቸዋለሁ። እሱን ተመግበው ከሞት ጋር የነበራቸውን ቀጠሮ ይሠርዛሉ።" ብለው ወደሁለቱ ዘወር ብለው

"ዐራት ዐይናው ቀለሙ የአቡሻህር ሊቅ ናቸው። ዘወትር በውስጣቸው የሚመላለሰው ሐሳብ የአቡሻኽር ቀመር ብቻ





ነው። የሥነ ፍጥረት ሊቅ ናቸው። ቅዳሜን በቀዳሚትነቷ ብቻ አይረዷትም። ምርምር ይጨምሩባታል። በዚሁ ዕለት ለሚወጡ ከዋክብት ጭምር ቀመር ይሰጧቸዋል። እሑድ ስትመጣ ደግሞ እንዲሁ ናቸው። ለቀኗ ምሥጢር ይፈልጉላታል። ምን አለፋችሁ! ዕለታትን የተለያዩ ቀመራትን ሲቀምሩ ነው የሚኖሩት። ሌሊት ተቀን እንቅልፍ አያውቁም፡ ፡ ዘወትር በውስጣቸው እየተኩተመተሙ ይኖራሉ።

ሌሊት ሌሊት አንድ ቀመር ጀምረው ፈለክ ፈለካትን ሲያሥሡ ወፎች "ጬጬጬጬ" ይላሉ።" ካሉ በኋላ "አሁን ደግሞ ወደማረፊያህ ውሰዳቸው።" ብለው ከርታታ ኮከቦችን ሸኝተው ወደምጣዱ ተመለሱ። እሳቱ እንደ ደመራ ይንገረገራል። ደቀኛውም የማር ሰፈፍ የመሰለውን ነገር ሲጋግሩ ከርታቶች ወደ ዐራት ዐይናው ማረፊያ ገሰገሱ።



Scanned with CamScanner

## ፴፩

መና ዘየረር

ወደ ዐራት ዐይናው ማረፊያ ሲያመሩ ታሪኩና ገሞራው በመደመም ላይ ነበሩ። በዚያ ላይ ከሴቶች መዳፍ መናውን ተቀብለው እስኪቀምሱ ጓጉተዋል። ከደቀኛው እስከ ዐራት ዐይናው ያለው ርቀት ግማሽ ሰዓት ይጨርስ ነበር። ውስጥ ለውስጥ ያለው ሥርጥ መንገድ ረጅም ነው። ጥቂት እንደ ገሰገሱ ገሞራውና ታሪኩ ስለ መናው አንዳንድ ምሥጢር ማንሣታቸው አልቀረም።

"ለመሆኑ ይህ የመና ቁራሽ መኻል ሀገር ድረስ አብሮ ይሄዳል? ወይስ ምግብነቱ በስዉሩ ዓለም ላሉት ጠቢባን ብቻ ነው?" አለ ገሞራው።

"የትም ቦታ ቢሄዱ መናው መና ነው። የተፈጥሮ መና ስለሆነ የሄትም ተጋግሮ ይበላል።" አሉ ዐራት ዐይናው ፊት ፊት እየቀደሙ ሁለቱን እየመሩ ሳለ።

"መኻል ሀገር ወሰደው አረጋግጠውታል የኔታዬ?" ታሪኩ በትሕትና ጠየቃቸው።

"በደንብ እንጂ።" አሉ ዐራት ዐይናው።





"ከዚህ በፊት ወዴት ሀገር ወስደው ተመግበውታል?" አለ ታሪኩ።

"ቋራ ሰባኬ ወንጌል መስዬ ከዛፍ ሥር ስውል ሳድር ምግቤ መናው ነበር። የረር ተራራም ከዋሻው ውስጥም እንዲሁ ለአንድ ዓመት ያኽል ቁጭ ብዬ ያለምንም ሥጋት ተመግቤዋለሁ። የክፉ ቀን ማለፊያ መሆኑን የተረዳሁት የረር ዋሻ ውስጥ ነው። ከመናው ጎን ለጎን መኻል ሀገር ስዋሬንም ለብዙ ቀናት የተጠቀምሁበት በዚሁ ዋሻ ውስጥ ነው። የረር ተራራ።" አሉ ዐራት ዐይናው።

"የረር ደግሞ ምን ሊሠሩ ሄዱ?" አለ ገሞራው

"እረ ጉድ ነው አያ! የመኻል ሀገሩ ሕዝብ ደግ ቀን የሚመጣው ደግ ንጉሥ ሲነግሥ ነው ብሎ ያምናል። ስሙንም ቴዎድሮስ ሲል ያነሣዋል። ሣልሳዊ ቴዎድሮስ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ በሕዝቡ ዘንድ ብቻ የሚነሣ ጥያቄ አይደለም። የቤተ ክህነት ሰዎችም በከፊል ያወራሉ። እሱ ሲመጣ የአንድ ላም ወተት የአንድ በሬ እሸት ለዓለም ይበቃል። የምድር በረከት ማለት እሱ ነው። ከየረር ተራራ ይወጣል ሲሉ ያሚርታሉ። መነሻው ከየረር መሆኑ ከታወቀ ተሰውሮ የሚኖር ከሆነ እንደእሱ ተሰውሬ እፈልገዋለሁ። በገሀዱ ዓለም የሚኖር ከሆነ ደግሞ አያመልጠኝም ብዬ ወደ



Scanned with CamScanner

የረር መንገድ ጀመርሁ::" አሉ ዐራት ዐይናው በስሱ ፈገግ ብለው::

"አዋቂው እንዳላዋቂ ይህን ተራ ወሬ ሰምተው ቴዎድሮስን ፍለጋ ይሄዳሉ እንዴ የኔታ?" አለ ታሪኩ::

"ይቅርታ ይደረግልኝ ወንድሜ! ሰው የሚኖረው በምኞት ዓለም ውስጥ ነው:: ይህ ዘመን ደግሞ ከእውናዊ ይልቅ በምልኪ የተመላ ዘመን ይመስለኛል:: ከደቂቀ ተዋነይ በቀር ሁሉም የአዲሱን ቴዎድሮስ ምጽአት ይጠብቃል:: ሁሉም በምናቡ የራሱ የሆነ ንጉሥ አንግሦ መኖር ከጀመረ ሰነባብቷል:: በዚህ ዘመን የመኻል ሀገር ሰዎች ቴዎድሮስ ይነግሣል ሲሉ ሰምቶ ዝም ማለት ደግሞ ነውር ነው:: ከእኛ ከጠቢባኑ በኩል እውነታውን ማወቅ ያስፈልጋል:: ሌሎች ተሰውሮ ይኖራል እያሉ ሕዝቡን ሲያጀጅሉ ዝም ብሎ መመልከት አግባብ አይደለም:: እናም በስዋሬ የሚኖር ከሆነ በስዋሬ ሆኜ እፈልገዋለሁ ብዬ የረር ከተፍ አልሁ::" ካሉ በኋላ አከሉበት::

"መቼስ የስዋሬ ጥበብ ለመቼ ይሆናል? በስዋሬ አሉ የሚባሉትን በስዋሬ ሆኖ ማረጋገጥ ደግሞ ከእኛ ከጠቢባኑ ይጠበቃል:: ወደ የረር ለመሄድ ያነሣሣኝ በስዋሬ አለ ስለተባለ ነበር:: እውነታውን ለማረጋገጥ ሄድሁ::" ብለው





ዕረፍት ሲያደርጉ ከትልቁ ዶቅማ ሥር ደገፍ አሉ:: ገሞራውና ታሪኩ በቀኝና በግራ በኩል ተኮልኩለው ማዳመጥ ቀጠሉ::

"ይህ ትንቢታዊ ንግርት ደግሞ ከጥንት ጀምሮ ሲነገር የመጣ ነገር ነው:: በተለይ በዘጠና ሰባት ዓመተ ምሕረት ቴዎድሮስ ሲነግሥ የረር ላይ ተገልጧል የሚል ወሬ በየስፍራው ተናፍሶ ነበር:: እኔም ወሬውን ስሰማ ከዚሁ ከጠቢባን ዓለም ወጥቼ ወደ የረር ለመሄድ ወሰንሁ:: ጓደኞቼ ተቃወሙ:: መሄድ አለብኝ ብዬ ከረርሁ:: ለምን መሄድ እንዳለብኝ ሲጠይቁኝ መኻል ሀገር ቴዎድሮስ ይነግሣል:: ከየረር ቴዎድሮስ ይነሣል እየተባለ ነው:: የረር ደርሼ እውነታውን መረዳት አለብኝ ብዬ ወደየረር ጉዞ ጀመርሁ:: ፈቀዱልኝ:: ከወር በኋላ የረር ከተፍ አልሁ::" ብለው ከዶቅማው ፍሬ ለቃቅመው ሰጧቸው:: ተቀብለው መግመጥ ጀመሩ:: ዐራት ዐይናው ግን ቀጠሉ::

"የረር ስገባ እንደእኔ ወሬ ሰምተው ወደ የረር የመጡ ሰዎች ብዙ ነበሩ:: አዲሱ ንጉሥ ግን በሀገሩ አልነበረም:: ቴዎድሮስ ሳይኖር በወሬ ብቻ ተራራው በወታደር ሲመነቀር አገኘሁት:: ወታደሮች በዚሁ ዋሻ እየዞሩ በየዋሻው ለጸሎት

መጥተው ፈጣሪያቸውን ደጅ የሚጠኑ አባቶችን ያስቃያሉ። ትዝ ይለኛል!።

ዘመኑ የወከባ ዘመን ነበር። ወከባው በዝቶ ሰው ሁሉ ተሰላችቶ ነበር። ወቅቱ ዐሥራ ዘጠኝ ዘጠና ሰባት ዓመተ ምሕረት የማቴምስ ዘመን ነበር። በወቅቱ መንግሥት ተናውጦ ነበር።" ካሉ በኋላ

"በእርግጥ ከመሄዴ በፊት ከጠቢባን አንዱ ተነሥቶ አሁን ያለው መንግሥት ገና ይቀጥላል። ከዚህ ዓመት ላይ አያቆምም። ይህን በሐሳበ ርቱዕ ቀመር ደርሼበታለሁ። ሕዝብ ያልቃል። መንግሥት ግን ይቀጥላል። አትሂድ ብሉ ሞግቶኝ ነበር። አሻፈረኝ ብዬ ነው የሄድሁት።" ሲሉ ከመካከል ሌላ ምሥጢር ጣል አደረጉ።

"ሐሳበ ርቱዕ ደግሞ ምን ዐይነት ቀመር ነው?" አለ ታሪኩ።

"ይህ የጥበብ ቀመር ነው። በደቂቀ ተዋነይ ዓለም ማንም ያውቀዋል። ቀመሩ የሒሳብ ቀመር ቢጤ ነው። ዘመናትን አሻቅቦ ይቆጥራቸዋል። አቆልቁሎም ያያቸዋል። አቆልቆሎ ሲቆጥር ከመጀመሪያ ጀምሮ በዘመናት ያለፉትን ክስተቶች ወደኋላ ሂዶ ያመጣቸዋል። አሻቅቦ ሲቆጥር ደግሞ ወደፊት በዓለም ያለውን መጻኢ ዘመን ኩልል አድርጎ ያመጣዋል።





ምጽአት ድረስ ያመጣል። የአንድን መንግሥት ፍጻሜ ጭምር የሚያመጣ የዘመን ቀመር ነው። ምሉዕ ሐሳቡን ከጠቢባኑ አንደበት በሌላ ቀን ትማሩታላችሁ።" ብለው ወደወጠኑት ሐሳብ ተመለሱ።

"በወቅቱ የነበረው መንግሥት እንደሚቀጥል እኔም አውቅ ነበር። ነገር ግን የረር ተራራ ላይ ወጥቼ ቴምድሮስ የሚባል በስዋሬ የሚኖር ንጉሥ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ አለብኝ ብዬ መንገድ ስጀምር ጓደኞቼ በእንባ ሸኙኝ። ሰተት ብዬ የረር ገባሁ። ስደርስ እንደኔው ሁኔታው አሳስቧቸው ከጎንደር ከጎጃም ከትግራይ ከወሎ ከወለጋ ከሸናሻና ከዚህ ከቅርቡ ኩንፈል ጭምር የሄዱ ሰዎች በየጥሻው ተሰክተዋል። በተለይ ከሸናሻና ከኩንፈል ከመጡ ከፊሉ ስዋሬ ጭምር ያውቃሉ። ከስዋሬ ውጪ ከሆኑት መካከል ደግሞ መርሻ ዘማይጣድ ቀዳሚው ነበሩ። እንደኔው ቴምድሮስን ኀሣሣ የረር መጥተው ቁጭ ብለዋል።" ብለው ሳቅ ሲሉ

"መርሻ! መርሻ! መርሻ ደግሞ ማን ናቸው?" አለ ታሪኩ።

"መርሻን አታውቃቸውም? ድፍን ጎንደርኮ ያውቃቸዋል።" አሉ ዐራት ዐይናው።

"እስኪ በደንብ ያስረዱኝ፡፡ ርእሰ መምህራን መርሻ የሚባሉ የተከሌውን የአቋቋም ሊቅ አውቃለሁ፡፡ ደብረ ታቦር ኢየሱስ የተክሌ አቋቋም ምስክር ቤት ጉባኤ አሳቸው፡፡

እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋቸው ደብረ ታቦር ቴዎድሮስ አደባባይ ነው፡፡ በዚህ አደባባይ የሊቃውንት ጉባኤ ተደርጎ እኔም እርሳቸውም የበዓሉ ተሳታፊ ነበርን፡፡ እርሳቸው በአቋቋም ሊቃውንት ታጅበው በዐሉን ሲመሩ ነበር፡፡ መምህሩ የወረብ ቀለም ለበዓሉ ሲያቀርቡ ለእኔ መወድስ ተሰጠኝ፡፡ በጭንቅ ተገፍቼ መወድስ ልቀኝ ስጀምር የጎንደር ሊቃውንት በጭብጨባ አጀቡኝ፡፡ ትዝ ይለኛል፡፡ ያን ቀን ትንሽ ወፈፍ አድርጎኝ ነበር፡፡ የቅኔ ስሜቴ ከቁጥጥሬ ውጪ ስለሆነ ወፈፌነት ሽው ብሎብኝ አለፈ፡፡ እንዲህ አይነት ነገር አልፎ አልፎ ይጀማምረኛል፡፡ በእርግጥ፣ የበጋውን መባቻ ብቻ ጠብቆ የሚከሰት ስሜት ስለሆነ ያንን ያኽል አሳሳቢ አይደለም፡፡ እናም ቴዎድሮስ አደባባይ በጎንደር ሊቆች ሲጨናነቅ ለእኔ መወድስ ተሰጠኝ፡፡ ከጎንደር ሊቆች ፊት መወድስ መዝረፍ አልፈለግሁም ነበር፡፡ በፍቅር ገፋፍተው የቅኔውን ዘረፋ አስጨበጡኝ፡፡ ከጎንደር ሊቆች ፊት ቆሜ እንደልማዴ ዐይኔን ጨፍኜ መወድስ ስዘርፍ ሊቁ መርሻ ከፊት ለፊቴ ቆመው ፈገግ ፈገግ ሲሉ ነበር፡፡ የቅኔ ሰው ስለሆኑ ሐሳቤን በደንብ እንደተረዱኝ ገብቶኛል፡፡





እንግዲህ እኔ የማውቃቸው መርሻ ይህንን ይመስላሉ፡፡ የዜማ፣ የአቋቋምና የቅኔ ሊቅ ናቸው፡፡ ሌላ መርሻ ግን አላውቅም፡፡" አለ ታሪኩ፡፡

"እኒህስ ሌላ መርሻ ናቸው፡፡ እንግዲህ በሀገራችን በርኩስ መንፈስ ይሁን በቅዱስ መንፈስ እየተመሩ አንዳንድ ትንቢታዊ ነገር የሚናገሩ ሰዎች እንደነበሩ እሙን ነው፡፡ ከእኒህ መሰል ሰዎች አንዱ ደግሞ የማይጣዱ መርሻ ነበሩ፡፡ መርሻ እስከዐሥራ ዘጠኝ ዘጠና ሰባት ዓመተ ምሕረት ድረስ በሕይወት እንደነበሩ አውቃለሁ፡፡" ካሉ በኋላ "አንተ አታውቃቸውም ማለት ነው?" አሉ አሁንም ወደታሪኩ ዘወር ብለው፡፡

"በርኩስ መንፈስ የሚመሩ ከሆነ አላውቃቸውም፡፡ በተለይ እኔ እኒህን መሰል ሰዎች አጥብቄ እፈራለሁ፡፡ መቅረብም አልወድም፡፡" አለ ታሪኩ፡፡

"በእርግጥ እኔም በመልክ ያየኋቸው በዐሥራ ዘጠኝ ዘጠና ሰባት ዓመተ ምሕረት የረር ዋሻ ውስጥ ነበር፡፡ በዚያ ላይ መርሻ ብዙ የሚያስፈሩ ሰው አይደሉም፡፡ እኔም መርሻን በአካል ከማግኘቴ በፊት ወሬአቸውን እሰማ ነበር፡፡ ስለ ርሳቸውም አንዳንድ ወጣ ወጣ ያለ ምሥጢር እሰማ ነበር፡፡



Scanned with CamScanner

ያ ነው ከመርሻ ጋር ሊያግባባን የቻለው፡፡" ሲሉ ወጉን ከሩቅ ጎተቱት፡፡

"እንዴት?" አለ ታሪኩ፡፡

"ባንድ ወቅት ደቂቀ ተዋነይ በኢትዮጵያ ካሉ ገዳማት ወደ አንዱ ልከውኝ ነበር፡፡ መልእክቱ በዚህ ገዳም ውስጥ አንድ ብርቅዬ መጽሐፍ እንዳለ ተሰምቶ ያንን ጽፌ ቅጅውን ወደዚህ ዓለም ለማምጣት ነበር፡፡ ልብሰ ምንኩስና ለብሼ ወደተላክሁበት ገዳም ገባሁ፡፡ ከገዳሙ እንደገባሁ መጋቢው ሃይማኖቴን ጠይቆ በአመክሮ እንድቆይ ነግሮ ተቀበለኝ፡፡ ከማኅበረ -ገዳሙ ጋር ኅብረት ስፈጥር ምን ምን ሙያ እንደምችል ተጠየቅሁ፡፡ ልብስ ስፌትና መጽሐፍ መጣፍ ነፍሴ ነው፡፡ በብራናም ሆነ በወረቀት ቁም ጽሑፍ መጣፍ እችላለሁ ስል ተናገርሁ፡፡ ቤተ-መጻሕፍት ለመቀላቀል ዓመታትን ማስቆጠር አለብህ ልብስ ስፌቱን ግን ቀጥል ብለው ከልብስ ስፌት ክፍል መደቡኝ፡፡ የልብስ መኪና ጠምጄ የመነኮሳቱን ቆብና ቀሚስ መስፋቱን ተያያዝሁት፡፡ ቆብና ቀሚስ ስዘመዝም አንድ እንግዳ ከማይጣድ መጣ፡፡ አዲስ መናኝ ነበር፡፡ ማኅበሩ በገዳሙ ሥርዓት ተቀብሎ ማረፊያ ሰጠው፡፡ መቅኑን ተቆነነ፡፡ ከማረፊያው ጎን ለጎን ሥርዐተ ገዳሙን መከተል ነበረበት፡፡ በገዳሙ ሥርዐት መሠረት





ከዓለም ሲመጣ ለብሶት የመጣውን ዓለማዊ ልብስ አውልቆ ልብሰ-ምንኩስና እንዲለብስ ታዘዘ፡፡ ለቀሚስና ለቆብ የሚሆን ቅዳጅ አቦጀዴ ተሰጠው፡፡ አቦጀዴው ብትን ጨርቅ ነበር፡፡ ያን ይዞ ቀሚስ ስፋልኝ ብሎ ወደእኔ መጣ፡፡ ቆብና ቀሚሱን እየሰፋሁ ስናወጋ "አንተ ወንድሜ ከወዴት መጥተህ ነው? አልሁት፡፡

"ማይ ጣድ ጊዮርጊስ"

"ለምን ዓለምን ንቀህ መነንህ?"

"ምናኔውን ፈልጌው አይደለም፡፡ በማይጣድ ጊዮርጊስ አንቱ የተባልሁ ገበሬ ነበርሁ፡፡ አርሼ አልደክምም ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን እርሻ ላይ ሳለሁ የጤና እክል ገጠመኝ፡፡ እጄ ደርሶ ልንቀስቀስ አለ ብሎ እጁን አውጥቶ አሳየኝ፡፡" ብለው ከንዳቸው አፈፍ አድርገው ማስረዳት ቀጠሉ፡፡

"ቀኝ እጁ ለብቻው ከባሕር ላይ እንደ በቀለ ቄጤማ ይንቀጠቀጣል፡፡ ይህ ከሆነ ለምን ወደ ጠበል አትሄድም? ለጤናህ ከገዳም ይልቅ ጠበል ለጠበል ብትዞር ይሻልህ ነበር ስለው ወደዚህ የመጣሁት መርሻ ልኮኝ ነው አለኝ፡፡ ሕማሙ እንደጀመረኝ መፍትሔ ፈልጌ ወደመርሻ ሄድሁ፡፡ ጠበል ይመራኛል ስል ወደዚህ ገዳም ሂድ እኔ በሰኔ ማርያም